# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 215 ሚያዝያ 5 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# “ያልተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታን ንግግር እንጂ ጦርነት አይፈታውም”

- አቶ ሞገስ ባልቻ
የዴሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ዘርፍ ኃላፊ ሚኒስትር

አዲሱ ገረመው



አዲስ አበባ፡- በየትኛውም የዓለም ክፍል ያለውን ያልተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ ንግግር እንጂ ጦርነት አይፈታውም ሲሉ የዴሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ዘርፍ ኃላፊ ሚኒስትር አቶ ሞገስ ባልቻ ገለጹ፡፡ አገራዊ ምክክሩ አገራዊ ተስፋ የሚሰጥ እንደሆነም ጠቅሰዋል፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የዴሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ዘርፍ ኃላፊ ሚኒስትር አቶ ሞገስ ባልቻ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደጠቀሱት፤ በየትኛውም የዓለም አካባቢ ያለውን ያልተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ የሚፈታው በጦርነት ሳይሆን በውይይት መድረክ ነው፡፡

ከጦርነት ይልቅ ንግግር ለመግባባት አዎንታዊ ሚና እንዳለው የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለያየ ማህበራዊ ትስስር ውስጥ ያለ በመሆኑ መለያየት እንደማይችል፤ መፍትሄው ደግሞ ተነጋግሮ አንድ መሆንና በተግባቦት ችግሮችን መፍታት የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠር ነው ብለዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ አገራዊ ምክክሩ ጠቃሚ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ የማያግባቡና ልዩነት ላይ ያሉ ጉዳዮችን ደግሞ በመከባበር መፍታት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ ልዩነት መከባበሪያ እንጂ መጠፋፊያ መሆን የለበትም ሲሉም ተናግረዋል፡፡

አካታች አጋራዊ ምክክር መድረኩም የፖለቲካ ጡዘቶችን በተወሰነ ደረጃ መልክ ያስይዘዋል ተብሎ እንደሚጠበቅም ገልጸዋል፡፡

“ያልተረጋጋ የፖለቲካ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






«ዓለም አቀፍ ተቋማትና የረድኤት ድርጅቶች በአፋርና አማራ ያለውን ከፍተኛ የሰብዓዊ ቀውስ ዘንግተውታል»

- አሜሪካዊቷ ጋዜጠኛ አን ጋሪሰን

ገጽ 4

# ክልሉ የሕዝብ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሦስት ወራት ዕቅድ አዘጋጅቶ መተግበር መጀመሩን ገለጸ

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ፡- አንገብጋቢ የሕዝብ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሦስት ወራት ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ መግባቱን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አስታወቀ፡፡

የክልሉ ብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ቢሮ ኃላፊ አቶ ይስሀቅ አብድልቃድር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ በብልጽግና ፓርቲ ጉባኤ በተቀመጡ አቅጣጫዎች ዙሪያ ከሕዝቡ ጋር ውይይት በማድረግ የሕዝቡን አንገብጋቢ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሦስት ወራት ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡

ፓርቲው በአስቀመጣቸው አቅጣጫዎች ዙሪያ ከሕዝብ ውይይት መደረጉን አመልክተው፤ ፓርቲው ያስቀመጣቸውና ሕዝብ ያነሳቸው ጥያቄዎችን ለመመለስ ሕዝቡ፣ መንግሥትና ባለድርሻ አካላት እጅና ጓንት ሆነው ዕቅዱን ለመፈጸም ወደ ተግባር መግባቱን ገልጸዋል፡፡

ክልሉ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ የሚካሄድበት

ክልሉ የሕዝብ ጥያቄዎችን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ይስሀቅ አብድልቃድር ፤












# “አማራ ባንክ የማዕከሉ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆኑ የደንበኞቹን አገልግሎት ያቀላጥፍለታል”

- ኢትዮ ቴሌኮም

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የአማራ ባንክ ዘመናዊ የሞጁላር መረጃ ማዕከል አገልግሎት ተጠቃሚ መሆኑ የባንኩን የደንበኞች አገልግሎት እንደሚያቀላጥፍለት ኢትዮ ቴሌኮም ገለጸ፡፡ ኩባንያው ለአማራ ባንክ ዘመናዊ የሞጁላር መረጃ ማዕከል አገልግሎት ለመስጠት የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረሟል፡፡

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ፍሬሕይወት ታምሩ ኩባንያቸው ከአማራ ባንክ ጋር የመግባቢያ የስምምነት ፊርማ ሲያካሂድ እንደገለፁት፤ ኢትዮ ቴሌኮም ለአማራ ባንክ ዘመናዊ የሞጁላር መረጃ ማዕከል አገልግሎት ለመስጠት የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረሟል፡፡ ስምምነቱ የባንኩን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት በዘመናዊና ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃውን በጠበቀ የመረጃ ማዕከል አማካኝነት አስተማማኝ አገልግሎት ለደንበኞቹ ለመስጠት የሚያስችለው ነው፡፡



ወይዘሪት ፍሬሕይወት ታምሩ

የዳታ ማዕከሉ ከፍተኛ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የገለጹት ሥራ አስፈፃሚዋ፤ ለላቀ የደንበኛ አገልግሎት ተሞክሮ የሚሆን፣ አዳዲስ ፕላትፎርምና አገልግሎትን ለማስጀመር የሚያስችል፣ ተለዋዋጭ (flexible) የቴክኖሎጂ ባህሪይ ያለው፣ ደንበኞች ለሚያካሂዱት ቢዝነስ አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሁም ከደንበኞች ጋር በፈጣን ሁኔታ ለመገበያየትና ለማስተናገድ የሚያስችል ሆኖ መደራጀቱንም ተናግረዋል፡፡

ማዕከሉ ደረጃውን የጠበቀ ኃይልን የሚቆጥብ የኤሌክትሪክ ሥርዓት፣ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ቆጣቢ፣ የማቀዝቀዣ ሲስተምና የደህንነት ካሜራዎች የተገጠሙለት ሲሆን ዘመናዊ የሆነ የኔትዎርክና የፋይበር ኬብል ማቀፊያዎች እና ኮምፓርትመንቶች ያሉት ነው ሲሉም ገልጸዋል፡፡

እንደ ወይዘሪት ፍሬሕይወት ገለጻ፤ የመረጃ ማዕከሉ የራሱ መጠባበቂያ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት አለው፣ በሰለጠነ የሰው ኃይል የሚመራ ከፍተኛ አቅም ያለው የዳታ ማዕከል ሲሆን፣ አገልግሎት እንዳይስተጓጎል የሚያስችል ሥርዓት ያለው ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የመረጃ ማዕከል ነው፡፡

ኩባንያው አገልግሎት ለሚሰጥባቸው ለሁሉም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና የኔትዎርክ መሠረተ ልማቶች አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ የተገነባ መሆኑም የተለየ ያደርገዋል ሲሉም ሥራ አስፈፃሚዋ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም ሁለት የሞጁላር ዳታ ማዕከላትን የገነባ ሲሆን፣ ተጨማሪ በግንባታ ላይ ካሉት ሦስት ማዕከላት ጋር በድምሩ አምስት የዳታ ማዕከላት በቅርቡ እንደሚኖሩት ተመልክቷል፡፡



# ኢንዱስትሪ ፓርኩ ወደ ውጭ ከላካቸው ምርቶች ከ4 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ አገኘ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ይርጋለም የተቀናጀ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ ወደ ውጭ ከላካቸው ምርቶች ከ4 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን የሲዳማ ክልል ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

የይርጋለም የተቀናጀ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ 11 ሸዶችን ይዞ ሥራ ከጀመረ አንድ ዓመት ያስቆጠረ ሲሆን፣ አሁን ላይ አምስት ኩባንያዎች በአቮካዶ ዘይት፣ በማር፣ ወተትና ቡና ምርቶች ላይ ተሰማርተው ለውጭ ገበያ በማቅረብ ገቢ በማስገኘት ላይ ናቸው።

የሲዳማ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መምሩ ሞኬ፤ ፓርኩ ወደ ሥራ ከገባ ጀምሮ እስካሁን ከአራት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማስገኘቱን ገልጸዋል።

ገቢው በፓርኩ በሚሠሩ ሁለት የአቮካዶ ዘይት አምራች ኩባንያዎች ከተላኩ ምርቶች የተገኘ መሆኑንም አብራርተዋል።

ኢንዱስትሪዎችን ከገበሬዎች እና ህብረት ሥራ ማህበራት ጋር በቀጥታ በማስተሳሰር የጥሬ ዕቃ ግብዓትና የምርት የግብይት ሰንሰለት መፈጠር መቻሉንና በፓርኩ ውስጥ ከሚገኙ ሁለት ፋብሪካዎች ጋር በተፈጠረ የገበያ ትስስር ከ135 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በቀጣይ ፓርኩ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ለመተካት ትኩረት እንደሚያደርግ ገልጸው፤ እሴት ተጨምሮባቸው ወደ አገር የሚገቡ የቡና እና የወተት ምርቶችን ለማስቀረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በይርጋለም የተቀናጀ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የተሟላ መሠረተ ልማት ያላቸውና አንድ መቶ ሃምሳ ኩባንያዎችን ማስተናገድ የሚችሉ ሼዶች ተዘጋጅተው ባለሀብቶችን በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውንም ዋና ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል።

ለፋብሪካው ግብአት የሚሆኑ የግብርና ምርቶች በስፋት ስለሚመረቱ፤ በርካታ የሰው ኃይል እና አስተማማኝ ሰላም ያለበት አካባቢ በመሆኑ ባለሀብቶች በፓርኩ ተጨማሪ ሥራዎችን እንዲጀምሩም ጥሪ አቅርበዋል።

በሲዳማ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ስር የሚተዳደረው የይርጋለም የተቀናጀ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ ተመርቆ ወደ ሥራ የገባው መጋቢት 4 ቀን 2013 ዓ.ም መሆኑ ይታወቃል።

# ብቁ የሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያ ለማፍራት ኢንዱስትሪውና የስልጠና ተቋማት በጋራ እንዲሠሩ ይደረጋል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በሆቴል ኢንዱስትሪው ተወዳዳሪና ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራት የሆቴል ኢንዱስትሪውና የስልጠና ተቋማት በጋራ እንዲሠሩ እንደሚደረግ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በትናንትናው ዕለት የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከጀርመን ልማት ትብብር ጋር በመተባበር ባዘጋጁት መድረክ ላይ በሆቴልና ቱሪዝም ሙያ ስልጠና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማበረታታት በሚቻልበት ሁኔታ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሂደዋል፡፡


ዶክተር በከር ሻሌ፤

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር በከር ሻሌ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ማዕከላት የሰለጠነና ሙያተኛ የሰው ኃይል እያመረቱ ለኢንዱስትሪው ቢያቀርቡም አሰልጣኝ ተቋማትና የሆቴልና ቱሪዝሙ ኢንዱስትሪው ዘርፍ በጋራ ስለማይሠሩ በሚቀርበው የሰው ኃይል እየረኩ አይደለም፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ የሆቴልና ቱሪዝም ተማሪዎችን የሚያሰለጥኑ ተቋማትና ሆቴሎች በጋራ እንዲሠሩ ይደረጋል፡፡

ከዚህ ቀደም ኢንዱስትሪዎቹ ምን ዓይነት ባለሙያ እንደሚፈልጉ ሳያውቁ የስልጠና ማዕከላቱ ባለሙያዎች የሚያሰለጥኑ በመሆናቸው በዘርፉ ከፍተኛ ችግር መኖሩንም ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ካሏት እምቅ አቅሞች መካከል የቱሪዝም መዳረሻዎች ዋነኞቹ ናቸው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በቂ የሰው ሀብት በመኖሩ በቂ ስልጠና በመስጠት ከአገር አልፎ በውጭ አገር በመሥራት ለአገር ገቢ ማስገኘት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ ሰፊ ሥራ ቢሠራም ስልጠናው የሚሰጥበት መንገድ ተገቢ ባለመሆኑ በሚፈለገው ልክ ውጤታማ እንዳልነበረ ገልጸዋል፡፡

ጥራት ያለውና ተወዳዳሪ የሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያ ባለመኖሩም የአገልግሎት ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ ሊጫወት የነበረውን የመሪነት ድርሻ ሳይጫወት እንዲቀር አድርጎታል ሲሉም አስረድተዋል፡፡


ከዚህ በፊት ሥርዓተ ስልጠናውና የሙያ ደረጃው የሚቀረጸው ኢንዱስትሪውን ወደ ጎን በመተው ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ የሆቴል ኢንዱስትሪውን ሳያሳትፍ የሚካሄድ ስልጠና በመጨረሻ ያልተጣጣመ የሰው ኃይል አቅርቦት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ ይህን ክፍተት ለመፍታት የኢንዱስትሪው ዘርፍና የስልጠና ተቋማት በትብብር እንዲሠሩ ይደረጋል ብለዋል፡፡

የግሉ ዘርፉ የተለያዩ ስልጠናዎችንና ድጋፎችን እንዲያደርጉ በማድረግም በዘርፉ ተወዳዳሪ የሆነ ባለሙያዎች እንዲፈጠሩ እንደሚደረግም አመልክተዋል፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ በዘርፉ ጥሩ ስልጠና ባለመኖሩ የተነሳ በገበያ ላይ ያሉ ሙያተኞችን ተፈላጊ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡ ይህ ብክነት በመሆኑ ማካካስ የሚቻለውና ዘርፉ በኢኮኖሚው እድገት ውስጥ ሰፊ ድርሻ እንዲኖረው ብቁ ባለሙያ ማፍራት ላይ በትኩረት ይሠራል፡፡

በአዲስ አበባ የጀርመን ኤምባሲ የጀርመን ትብብር ልማት ምክትል ኃላፊ ቤንጃሚን ሀከር በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በቱሪዝም ብዙ ሀብት አላት፤ ያላትን ሀብት አውጥታ እንድትጠቀም የጀርመን መንግሥት ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል፡፡

የጀርመን መንግሥት ዘርፉ ለአገር ኢኮኖሚ እንዲጠቅም በቴክኒክ፣ በገንዘብና በማማከር ረገድ ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል፤ በቀጣይም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል፡፡



አቶ ቢተው ሸባባው፤

# በዘንድሮው ክረምት በደን ለመሸፈን ከታቀደው ከ448 ሺ በላይ ሄክታር መሬት መለየቱ ተጠቆመ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በመጪው ክረምት በደን ለመሸፈን ከታቀደው 800ሺ. ሄክታር መሬት ውስጥ 448 ሺ. 468 ሄክታር መሬት ለችግኝ ተከላ መለየቱን የኢትዮጵያ ደን ልማት አስታወቀ፡፡ እስካሁን ባለው መረጃ ሁለት ነጥብ 738 ቢሊዮን የደን ችግኝ ተፈልቶ መዘጋጀቱ ተጠቁሟል፡፡

በኢትዮጵያ ደን ልማት የደን ልማት ዳይሬክተር ጀነራል አቶ ቢተው ሸባባው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሚቀጥለው ክረምት በደን ይሸፈናል ተብሎ ከታቀደው ስምንት መቶ ሺ. ሄክታር መሬት መካከል እስካሁን በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች 448 ሺ. 468 ሄክታር መሬት ለችግኝ ተከላ ተለይቷል።፡

በዚህ ዓመት እንደ አገር የደንና የአገሮ ፎረስተሪው ችግኝ ተዳምሮ ስድስት ቢሊዮን ችግኝ ተፈልቶ ይተከላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በደን ችግኝ በኩል ይለማል ተብሎ በዕቅድ የተያዘው አራት ቢሊዮን ችግኝ ሲሆን እስካሁን ባለው መረጃ ሁለት ነጥብ 738 ቢሊዮን ችግኝ ተፈልቶ ለተከላ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህም የእቅዱን 71 በመቶ ነው፡፡ እስካሁን በሁሉም ክልሎች በተገኘው መረጃ መሠረት አራት መቶ 15 ቶን የችግኝ ዘር መጠቀም ተችሏል ብለዋል፡፡

ችግኞች እየተፈሉ እየተዘጋጁ የሚገኙት በአንድ መቶ ሦስት ሺ. 472 የችግኝ ጣቢዎችን በመጠቀም መሆኑን የጠቆሙት ዳይሬክተር ጀነራሉ፤ ተፈልተው እየተዘጋጁ ያሉ ችግኞችን የመቁጠሩ ሂደት እንዳልተጠናቀቀም ገልጸዋል፡፡

ሕዝቡ የደን ልማት ጥቅምን በመረዳቱ በየዓመቱ የሚተከሉ ችግኞችን በመንከባከብ እንዲጸድቁ በማድረግ ረገድ ውጤታማ ሥራ እየታየ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ እስካሁን ለደን ተከላ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች 448 ሺህ 468 ሄክታር መሬት ተለይቷል፡፡ ይህም የእቅዱን 50 በመቶ መሳካት ያሳያል ብለዋል፡፡

የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሩ ውጤታማ እንዲሆን የባለፈው ዓመት ተሞክሮ ሚኒስትሮች የተካተቱበት በግብርና ሚኒስቴር መሪነት በቀድሞው አካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ጸሐፊነት የሚመራው አብይ ኮሚቴ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ቢተው፤ በዚህ ዓመትም አብይ ኮሚቴው ይቀጥላል ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ የማይበገር የተቀናጀ የአረንጓዴ ልማትን ለማስፋት በጉልህ እየሠራችው ያለው የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ውጤት እየታየበት ነው፡፡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ባለፉት ሦስት ዓመታት ብቻ ከ17 ቢሊዮን በላይ ችግኝ በመላ አገሪቱ መትከል ተችሏል፡፡

# ልዩነቶችን ለሁለንተናዊ እድገት ለማዋል የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል ሚኒስቴሩ ገለጸ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የሚታዩ የቋንቋ፣ የባህልና ሌሎች የልዩነት እሴቶችን ለሁለንተናዊ እድገት ለማዋል የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

ሚኒስትሩ አቶ ቀጀላ መርዳሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በልዩነት ውስጥ የአንድነትና የወንድማማችነት እሴቶችን ማጉላት ለአገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት ወሳኝ ነው፡፡

ብዝሃነት ለአንድ አገር የውበት ምንጭና የተለያየ ተፈጥሯዊ ማንነት መገለጫ ሆኖ ሳለ ባለፉት ዓመታት ከአንድነትና ከወንድማማችነት እሴቶች ይልቅ በልዩነት ላይ ሰፊ ሥራ በመሠራቱ በአሁኑ ጊዜ ብዝሃነታችን የጭቅጭቅ ምንጭ ሲሆን ይታያል ብለዋል፡፡

በቴክኖሎጂና በኢኮኖሚ እድገት ቀዳሚ ተርታ ላይ የሚሰለፉ እንደ አሜሪካና ካናዳ ያሉ አገሮች ለአንድነትና ወንድማማችነት ቅድሚያ በመስጠታቸው የባህልና የቋንቋ ልዩነት ጉዳያቸው እንዳልሆነ የተናገሩት አቶ ቀጀላ፤ በተለይ ካናዳ ውስጥ የፍራንኮፎን ወይም ፈረንሳይኛ ተናጋሪና አንግሎፎን ወይም እንግሊዝኛ ተናጋሪ በቋንቋና በባህል ልዩነት ሳይነታረኩ ልዩነትን በጸጋ ተቀብለው በአንድነት በሠሩት ሥራ የሚኮሩበት አገር ለመገንባትና ለማሳደግ መቻላቸውን አስገንዝበዋል።



አቶ ቀጀላ መርዳሳ፤

በኢትዮጵያም ኅብረብሔራዊ የፌዴራሊዝም ሥርዓት መከተል ከጀመረች ሦስት አስርት ዓመታት ማስቆጠሯን ያወሱት ሚኒስትሩ፤ ይህ ግን በትክክል ባለመተግበሩ ልዩነት የፖለቲካ መልክ በመያዝ የመነታረኪያ ምንጭ ሲሆን ታይቷል፡፡ ሆኖም ሕዝቡ ከጥንት ጀምሮ ቋንቋ፣ ባህልና የተለያዩ እሴቶች ተጋርቶ አብሮ የመኖር ባህሉ የቆየ ነው፡፡

ይህን አብሮ የመኖር እሴት መሠረት በማድረግ የተለያዩ ባህልና ቋንቋ ያላቸውን የአገሪቱን ሕዝቦች ሚኒስቴሩ ለማስተዋወቅ ራሱን የቻለ ክፍል በማቋቋም በትጋት እየሠራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ቀጀላ፤ የእርስ በእርስ ባህልና ቋንቋን ማወቅ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው በመገንዘብ ኅብረተሰቡ ሚኒስቴሩ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ተባባሪ እንዲሆን ጠይቀዋል።

ሚኒስቴሩ በቀጣይ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ጥናት ለማካሄድ እቅድ መያዙን ጠቅሰዋል፡፡

ከኢትዮጵያ በላይ በርካታ ብሔር ብሔረሰቦች ያሏቸው እንደ ሕንድና ናይጀሪያ ያሉ አገሮች ልዩነቶቻቸውን በአግባቡ በማስተናገድ አንድነታቸውን አጉልተው ለሁለንተናዊ እድገት ማዋላቸውን በአብነት ያነሱት አቶ ቀጀላ፤ በኢትዮጵያም ያሉ ልዩነቶችን ለገጽታና ለኢኮኖሚ ግንባታ ለማዋል የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ ቀጀላ ማብራሪያ፤ በኢትዮጵያ ትግል ታሪክ ጎልቶ ሲወሳ የነበረው የማንነት፣ የቋንቋ፣ የባህልና የሌሎች እሴቶች ጥያቄ ከሞላ ጎደል መልስ አግኝቷል። ጥያቄው ሕዝቦቹ ባደረጉት መራራ ትግል መመለሱ ትልቅ ድል ሆኖ ሳለ ልዩነትን በማክበር አንድነትን ማጠናከር ደግሞ ሌላ ፈተና እየሆነ መጥቷል ብለዋል። ሕዝቡን የማስተዋወቅና የማቀራረብ ሥራ በተገቢው ባለመሠራቱ ከወንድማማችነት መገፋፋትና መነቋቆር ገዝፎ ይታያል። መፍትሄው ልዩነትን በመቀበል አንድነትን ማጠናከር ብቻ እንደሆነም መክረዋል፡፡

# በክልሉ ለሚገኙ 71 ሺህ ተፈናቃዮች ድጋፍ መደረጉን ኮሚሽኑ አስታወቀ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ለሚገኙ 71 ሺህ ተፈናቃዮች በመንግሥት፣ በአካባቢው ማኅበረሰብ እና በአጋር አካላት ቅንጅት የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ መደረጉን የአደጋ ሥራጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ደበበ ዘውዴ እንደገለጹት፤ በአማራ ክልል ለሚገኙ 71 ሺህ ተፈናቃዮች ከ41 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ለአንድ ወር ቀለብ የሚያገለግል 10 ሺህ 603 ኩንታል ምግብ ለተፈናቃዮች እንዲከፋፈል ተደርጓል።

በተጨማሪም 28 ሺህ 625 ልዩ ልዩ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ከኮሚሽኑ ክምችት ላይ ተቀናሽ ተደርጎ ለመጠለያ ካምፖቹ ተሠራጭቷል፡፡ ኮሚሽኑ 3 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር ለእነዚሁ ካምፖች ለወጪ እንዲውል ወደ ክልሉ እንዲላክ ማድረጉንም አቶ ደበበ ተናግረዋል፡፡

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ከአላማጣ ከተማ፤ ከአላማጣ ዙሪያ ከኮረም፣ ከአፍላ፣ ራያ ባላ፣ ዛታ እንዲሁም ከራያ ቆቦ ገጠር ቀበሌዎች ተፈናቅለው በራያ ቆቦ ከተማ በተለያዩ አምስት የመጠለያ ጣቢያዎች እና በኅብረተሰቡ ውስጥ ተጠልለው 56 ሺህ 701 ተፈናቃዮች የሚገኙ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በተመሳሳይ በዋግ ኽምራ ዞን ፃግብጅና አበርገሌ ወረዳዎች ከሁሉም ቀበሌዎች፤ ከዝቋላ ወረዳ ስድስት ቀበሌዎች፤ ከሰቆጣ ዙሪያ አንድ ቀበሌ የተፈናቀሉ ዜጎች ቁጥር 67 ሺህ 488 ዜጎች መኖራቸውን አክለዋል። ከዚህ ውስጥ 49 ሺህ 184 ያህሉ በሰቆጣ ከተማ በጊዜያዊ መጠለያና በኅብረተሰቡ ውስጥ ተጠልለው፤ 18 ሺህ 304 ወገኖች ደግሞ በፅታ ከተማ በጊዜያዊ መጠለያ ይገኛሉም ብለዋል፡፡

መንግሥት የሚፈናቀሉ ዜጎችን ለመቀበል ተጨማሪ ካምፖችን እየገነባ መሆኑን እና በዚህም በሰሜን ወሎ ዞን ሀብሩ ወረዳ አካባቢ 88 ሺህ ሰዎች መያዝ የሚችል 400 ሄክታር መሬት ላይ ጊዜያዊ መጠለያ ዝግጁ መደረጉ ተናግረዋል፡፡

ቆቦ የሚገኙ ተፈናቃዮች ሀብሩ ላይ መጠለያ በማዘጋጀት ወደዚሁ መጠለያ እንዲገቡ ተደርጎ 16ሺ. 211 ወገኖች እስካሁን ወደ ተዘጋጀው ሳይት መግባታቸው



አቶ ደበበ ዘውዴ፤

ተገልጿል፡፡

በተመሳሳይ በደቡብ ወሎ ዞን ሐይቅ ከተማ ጃሬ በተባለ አካባቢም ከ5 ሺህ እስከ 10 ሺህ መቀበል የሚችል ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያ ተሠርቶ እስካሁን 477 ተፈናቃዮችን ተቀብሎ እያስተናገደ ነው ተብሏል።

በዋግ ኽምራ ዞን በሰቆጣ ከተማ ወለህ በተባለ አካባቢ 10 ሺህ ሰዎችን ማስተናገድ የሚችል 45 ሄክታር መሬት ላይ ጊዜያዊ መጠለያ ዝግጁ መደረጉን እና 1 ሺህ 731 ወገኖች ወደ ሳይቱ እንዲገቡ መደረጉን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

ተፈናቅለው የሚመጡ ዜጎችን ከመቀበል ጎን ለጎን መመገቢያ ቁሶች፣ የአልባሳት አቅርቦት እንዲሁም ውኃና መፀዳጃ፣ ጤና እና ሌሎች አገልግሎቶችን እንዲሟሉ መንግሥት በቅንጅት እየሠራ ነው፡፡

ይህንኑ ተግባር ለማስፈጸም የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን ባለው ልምድ በመጀመሪያ ደረጃ በአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል ባሕር ዳር ላይ ማቋቋሙን እና በየዞኑና በመጠለያ ብዙ ወገኖች ባሉባቸው አካባቢዎች በአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ኮማንድ ፖስት በማቋቋም ከምግብ ባሻገር የጤና፣ የውኃ፣ የፅዳት እና ሌሎችን አቅርቦቶች እንዲያሟሉ አልፎ አልፎ ችግሮች ቢኖሩም በቅንጅት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ግምታቸው 30 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ ለመጠለያነት የሚያገለግሉ 15 ጅምላ፣ 59 መካከለኛ፣ 6039 ፕላስቲክ እና ሌሎች አነስተኛ ድንኳኖች በክልሉ ለሚገኙ መጠለያ ካምፖች ከአደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን ክምችት ክፍል ወጪ ተደርጎ ሥርጭቱና ተከላው በተሳካ ሁኔታ መከናወኑንም ጠቅሰዋል፡፡

በተጨማሪም የውኃና ሳኒቴሽን አገልግሎቶች እንዳይቋረጡ አጋር አካላት በድጋፍ በአቀረቧቸው የውኃ ቦቴ ተሽከርካሪዎች እና የውኃ ማጠራቀሚያ ታንከሮች አማካኝነት ውኃ ለተፈናቃዮች ተደራሽ እየተደረገ መሆኑን የተናገሩት አቶ ደበበ፤ በመጠለያ ካምፖቹ 34 የሚሆኑ የጤና ባለሙያዎች አገልግሎት እየሰጡ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡

# «ዓለም አቀፍ ተቋማትና የረድኤት ድርጅቶች በአፋርና አማራ ያለውን ከፍተኛ የሰብዓዊ ቀውስ ዘንግተውታል»

*- አሜሪካዊቷ ጋዜጠኛ አን ጋሪሰን*

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፍ ተቋማትና የረድኤት ድርጅቶች በአፋርና በአማራ ክልል ያለውን ከፍተኛ የሰብዓዊ ቀውስ ዘንግተውታል ስትል አሜሪካዊቷ ጋዜጠኛ አን ጋሪሰን ተናገረች። ሂዩማን ራይትስዎችና አምነስቲ ኢንተርናሽናል በቅርቡ በሰሜኑ ኢትዮጵያ ያወጡት ሪፖርት ፖለቲካዊ ይዘት እንዳለው አስታውቃለች።

አን ጋሪሰን በኢትዮጵያ በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች ያደረገችውን ጉብኝት አስመልክቶ ከኢዜአ ጋር በነበራት ቆይታ ጦርነቱ ከፍተኛ የሰብዓዊ ቀውስ ማስከተሉን ገልጻለች።

ዓለም አቀፍ ተቋማትና የረድኤት ድርጅቶች በአፋርና በአማራ ክልል ያለውን ከፍተኛ የሰብዓዊ ቀውስ ሊገነዘቡና አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርጉ እንደሚገባ ተናግራለች።

አሸባሪው ሕወሓት በሰው ሕይወት ላይ ካደረሰው ጉዳት በተጨማሪ የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን ማውደሙንና ይህም በርካታ ሰዎች በሰብዓዊ ቀውስ ውስጥ እንዲቆዩ አድርጓቸዋል ብላለች።

ይህንንም ተከትሎ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በሕዝቡ ላይ የፈጸመው ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት እጅግ አሰቃቂ መሆኑን ተዘዋውራ በተመለከተቻቸው ሥፍራዎች ባደረገችው ምልከታ ማረጋገጧን ጠቁማለች።

ያም ሆኖ ዓለም አቀፍ ተቋማትና የረድኤት ድርጅቶች በአማራና በአፋር ክልል ያለውን የሰብዓዊ ቀውስ



ዘንግተውታል፤ የሚያደርጉትም ድጋፍ ከሚጠበቀው በታችና ሁሉን አቀፍ አለመሆኑን ገልጻለች።

በኢትዮጵያ ያለው የሰብዓዊ ቀውስ በትግራይ ብቻ ሳይሆን በአፋርና በአማራ ክልል ጭምር መሆኑ በመገንዘብ ዓለም አቀፍ ተቋማቱ ድጋፍ ሊያደርጉ እንደሚገባ ተናግራለች።

በሌላ በኩል ሂዩማን ራይትስ ዎች እና አምነስቲ ኢንተርናሽናል በቅርቡ በሰሜኑ ኢትዮጵያ ተከስቷል ያሉትን የሰብዓዊ መብት ጥሰት በተመለከተ ያወጡት የጋራ ሪፖርትም ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ነው ስትል ተችታዋለች።

ሪፖርቱ የወጣው የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በጉዳዩ ላይ ያጠናውን ሪፖርት ከመለቀቁ ከቀናት በፊት መሆኑን አንስታ፤ ይህም አንድ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት በማለም የተደረገ መሆኑን ገልጻለች።

ከዚህም በላይ ሪፖርቱ የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ ማዕቀብ እንዲጥሉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸትና ማዕቀብ ካልተጣለ በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ሊባባስ ይችላል የሚል እምነት በሰዎች ውስጥ እንዲያድር ያለመ መሆኑንም ነው የተናገረችው።

ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናልና የዓለም ጤና ድርጅት በኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብ እንዲጣል በአሜሪካን መንግሥት ውስጥ ያሉ የአንዳንድ ግለሰቦች ፍላጎትን ለማስፈጸም እየሠሩ መሆኑንም ጠቁማለች።

በተለይም የዓለም ጤና ድርጅት ዳይሬክተር ጄነራል የሆኑት ዶክተር ቴዎድሮስ አድሃኖም ስለ ትግራይ የሰብዓዊ ቀውስ ብቻ በተደጋጋሚ የሚያደርጉት ውግንና የፖለቲካ አቋማቸውን አመላካች ነው፣ ይህም ገለልተኛ በመሆን ድርጅቱን ለመምራት ከገቡት ቃል ጋር የሚጻረር ነው ብላለች።

አሜሪካዊቷ ጋዜጠኛዋ አን ጋሪሰን የመስክ ምልከታዋን መረጃ በማጠናቀር በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊ ቀውስና ሌሎች ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ትክክለኛ መረጃዎች በማሰራጨት ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የኢትዮጵያን ዕውነታ እንዲረዳ የበኩሏን እንደምትሠራ አረጋግጣለች።

## "ያልተረጋጋ የፖለቲካ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እንደ ኃላፊ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ውይይት ማድረግ ከተቻለ፣ ሕዝቡን ማሳተፍ ከተቻለ፣ የፖለቲካ ኃይሎች ሀሳባቸውን አቅርበው በዚህ ጉዳይ ላይ መናጋገር ከቻሉ የማያግባባቸው ጉዳይ አይኖርም ብለዋል፡፡

«ምክክሩ ትልቅ ተስፋ የሚሰጥ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን የጋራ ቤት የምንገነባበት ስለሆነ ያገባኛል በሚል እሳቤ አዎንታዊ ሚና ልንጫወት በምንችልበት መልኩ መሰለፍና ማገዝ ይገባል፡፡ ለዚህ የበኩላችንን ታሪካዊ ኃላፊነት መወጣት ይኖርብናል» ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ከአገራዊ ምክክሩ ባሻገር ሁሉም ሰው በትብብር መሥራት ከቻለ ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተስፋ ያላትና ውጤት ማምጣት የምትችል አገር ትሆናለች ብለዋል፡፡

ያጋጠሙ ፈተናዎች ያልፋሉ ያሉት አቶ ሞገስ፤ ባለፉት አራት ዓመታት ያሉ ሁኔታዎች ሲታዩ በአንድ በኩል ተፈጥሮ በሌላ በኩል ደግሞ ፖለቲካና የጥፋት ኃይሎች ፈተናዎችን ተሻግረናል፤ ይህም የኢትዮጵያን መጻኢ ጊዜ ጥሩና ተስፋ ሰጪ መሆኑን እንደሚያሳይ ጠቁመዋል፡፡

ለዚህም ሁሉም ሰው እጅ ለእጅ ተያይዞ በቋንቋ፣ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በአካባቢ ከመገፋፋት፣ እንዲሁም ወገንን ከመጥላትና ጭፍን ከሆነ አስተሳሰብ በመውጣት በወንድማማችነትና እህትማማችነት ስሜት አብሮነትን ሊያሳይ እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

ኢትዮጵያውያን የጋራ ቤትና የጋራ አገር ብለው መንቀሳቀስ ከቻሉ ኢትዮጵያ ከራሷ ሕዝብ አልፋ ለምሥራቅ አፍሪካ ዜጎች ልትበቃ የምትችል ናት ብለዋል።

# በላልይበላ በቱሪዝም ገቢ ይተዳደሩ የነበሩ አገልጋዮችና ነዋሪዎች ችግር ላይ መውደቃቸው ተገለጸ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በደብረ ሮሃ ቅዱስ ላልይበላ ገዳም በቱሪዝም ገቢ ይተዳደሩ የነበሩ አገልጋዮችና የአካባቢው ነዋሪዎች ችግር ላይ መውደቃቸውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ገለጸች።

የተለያዩ ተቋማት ለላልይበላ ገዳም አገልጋዮችና ለአካባቢው ነዋሪዎች ድጋፍ እንዲያደርጉ ተጠየቀ።

የሰሜን ወሎ፣ የደቡብ ወሎና የከሚሴ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤርሚያስ ትናንት እንደገለጹት፤ የቅዱስ ላልይበላ ከተማዋም ሆነ ገዳሙ የሚተዳደረው በቱሪዝም ገቢ ነው። ላለፉት ሁለት ዓመታት በተፈጠረው የኮሮና በሽታና በሰሜን ኢትዮጵያ በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት የቱሪዝም ገቢው በመዳከሙ የገዳሙ አገልጋዮችና ነዋሪዎች ለችግር ተጋልጠዋል።

በተለይም የቅዱስ ላልይበላ አስራ አንድ አብያተክርስቲያናትን የሚያገለግሉ ከአንድ ሺህ በላይ ካህናት፣ ከአንድ መቶ በላይ ቅርሱን የሚጠብቁ ሠራተኞች፤ እንዲሁም ከ800 በላይ የአብነት ተማሪዎችና ከ200 በላይ አረጋውያንና ወላጅ አልባ ሕፃናት የችግሩ ዋነኛ ተጠቂዎች ሆነዋል ብለዋል።

ከ10 ሺህ በላይ የሚሆኑት ዜጎች ከገዳሙ በቀጥታ የወር ደመወዝና የዕለት ምግብ የሚያገኙ መሆኑን ገልጸው፤ ገዳሙም በእራሱ የሚተዳደረው ቅርሱን በሚጎበኙ ጎብኚዎች በሚከፍሉት የመግቢያ ክፍያ ነው። ይህ ሲቀር የአካባቢው ሁኔታ ይበልጡኑ አደጋ ውስጥ ወድቋል ሲሉ አስረድተዋል።

ከዚህ ባለፈ በጦርነቱ ምክንያት በአካባቢው ያሉት መሠረተ ልማቶች አገልግሎት እየሰጡ አይደለም ያሉት ብፁዕ አቡነ ኤርሚያስ መብራትና ውሃ አለመኖሩን ጠቁመዋል።

የምግብ ማብሰያና ወፍጮ ፍለጋም ነዋሪዎች ከ50 እና 60 ኪሎ ሜትር በላይ መጓዝ ግዴታ እንደሆነባቸው አስታውቀዋል።

ከባለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ በተከሰተው የኮሮና ወረርሽኝና በጦርነቱ ምክንያት እንደ ከዚህ በፊቱ በቱሪዝም የሚገኘው ገቢ ባለመኖሩ ለችግር ለተዳረጉ ዜጎች ድጋፍ እንዲደረግ ጥሪ አቅርበዋል።

በሰሜን ወሎና በዋግኽምራ ዞኖች ከሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም ጀምሮ በጦርነቱ ምክንያት በደረሰው ውድመት ከቱሪስት ገቢ የሚገኘው ገቢ ተቋርጧል። በዚህም ለተደራራቢ ችግር ለተጋለጡ ዜጎች የተለያዩ ተቋማት ድጋፍ ማድረግ ይገባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

በአካባቢው ባለው ችግር ምክንያት የዓለም አቀፍ ቅርሱ ጠባቂዎች እየተሰደዱ መሆኑን ጠቁመው፤ በተጨማሪ የማይዳሰስ ቅርስ የሆነውን መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያቀርቡ ካህናትም እየተሰደዱ ነው



አባ ጽጌሥላሴ መዝገቡ፤ ብፁዕ አቡነ ኤርሚያስ ፤

ብለዋል።

መንፈሳዊ አገልግሎቱን ለማየት ይመጡ የነበሩ ቱሪስቶች አሁን ላይ ቦታውን እየጎበኙ ባለመሆኑ ችግሩ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን አስታውቀዋል።

የቱሪዝም ገቢው እስኪጀመር በአገር ውስጥና በውጭ አገራት የሚገኙ ዜጎች እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ድጋፍ እንዲያደርጉም ጠይቀዋል።

የቅዱስ ላሊበላ ገዳም ዋና አስተዳዳሪ አባ ጽጌሥላሴ መዝገቡ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በኮቪድና በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተከሰተው ጦርነት የተነሳ ከላልይበላ አካባቢ ከ15 ሺህ በላይ ሰዎች ለስደት ተዳርገዋል።

የተለያዩ ደጋፊዎችና የመንግሥት አካላት ምግብና መድሐኒት ያለቀባቸውን አባቶች ከመደገፍ ጀምሮ ሲያደርጉ የቆዩት ድጋፍ የማይረሳ ነው ያሉት አስተዳዳሪው፤ አሁንም በተለይ መብራትና ውሃ ማግኘት ባለመቻሉ ከፍተኛ ችግር የወደቀውን ሕዝብ መደገፍ ይገባል ብለዋል።

በቱሪዝም ገቢ ማነስ የተጎዳውን የገዳሙን ማህበረሰብ ለመደገፍ በኢትዮ ቴሌኮም በኩል የገቢ ማሰባሰቢያ የአጭር ጽሑፍ መልክዕት አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ ሂደት መጀመሩንም ገልጸዋል።

መንግሥትና ዓለም አቀፍ ተቋማትም ቅርሱንና በቅርሱ ዙሪያ ያሉ ዜጎችን ሕይወት ለመታደግ ተገቢውን እገዛ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

## ክልሉ የሕዝብ ጥያቄዎችን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከመሆኑም አንጻር የተለያዩ ጸረ ሰላም ኃይሎች ፍላጎታቸውን የሚያንጸባርቁበት መሆኑን አመልክተው፤ ሸኔና በርታ ነፃ አውጪ የተሰኘው ቡድንና ሌሎች ጸንፈኞች ኃይሎች በሰላማዊ ዜጎች ጥቃት ማድረሳቸውንና የአካባቢውን ጸጥታ እያወኩ እንደሚገኙም ተናግረዋል፡፡

በተለይ ሸኔ በምዕራብ ወለጋ በኩል ወደ ክልሉ ሰርጎ በመግባት መንገድ በመዝጋትና በንጹሀን ላይ ጥቃት በማድረስ የክልሉን ሠላም እያደፈረሰ እንደሚገኝ ገልጸው፤ በሸኔና በሌሎች በጸረ ሠላም ኃይሎች ምክንያት 10ሺ የሚሆኑ ዜጎች ከቀያቸው መፈናቀላቸውን አስታውሰዋል፡፡

በሦስት ወራት እቅዱም የፀጥታ መዋቅሩና ሕዝቡ በመቀናጀት በክልሉ ሠላምና ጸጥታ በማረጋገጥ ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

ሠላምና ፀጥታን ለማረጋገጥ ከአጎራባች ክልሎች ጋር በጋራ መሥራት እንደ አቅጣጫ እየተሠራበት መሆኑን ጠቁመው፤ ክልሉ ሠላምና ፀጥታን ለማረጋገጥ አስተዳደር ወሰን አካባቢ የሚኖሩ ሕዝቦችን የልማት ተጠቃሚ ለማድረግ የጋራ ጽሕፈት ቤቶችን በማቋቋም እየተሠራበት መሆኑን አመክልተዋል፡፡

ፀረ ሠላም ኃይሎች በሚያደርሱት የሠላምና ጸጥታ ችግሮችና ከዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ የተፈጠረውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋትም የሦስት ወራት ዕቅዱ ትልቅ ሚና እንዳለው አመልክተዋል። ገበያውን ለማረጋጋት የተለያዩ ምርቶችን ሰብስቦ የሚያከማቹ ሕገወጥ ነጋዴዎች ላይ ሕግ እርምጃ እንደሚወሰድ ጠቁመው፤ መንግሥትም ገበያውን ሊያረጋጉ የሚችሉ የፍጆታ ዕቃዎችን በማቅረብ የበኩሉን ሚና እንደሚወጣም ተናግረዋል።

ሌብነትን መዋጋትን ጨምሮ ሌሎች የሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ በሦስት ወራት ዕቅድ ውስጥ ተካተው የሚሠሩ መሆኑን ጠቁመው፤ ዕቅዱን ተፈጻሚ የሚያደርግና ተፈጻሚነቱን የሚከታተል የተለያዩ ኮሚቴዎች መቋቋማቸውን አስረድተዋል፡፡

ኮሚቴዎቹም ከሕዝብ የተነሱ ጥያቄዎችና የብልጽግና ፓርቲ ያስቀመጣቸውን አቅጣጫዎች መሠረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ተቋማት ተቆጥሮ የተሰጡ ጉዳዮችን ለተፈጻሚነታቸው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል፡፡

የሕዝቡ ጥያቄዎች እንዲፈቱም ሕዝቡን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ አቶ ይስሀቅ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ራሳችንን ለምህረትና ይቅርታ ማዘጋጀት ይኖርብናል!

የጾም ወቅት ድህነት የሚገኝበት፣ ከፈጣሪ ጋር የመቀራረቢያ ጊዜ መሆኑ በሁሉም የሃይማኖት አስተምህሮዎች ከፍ ብሎ የሚነገር ትምህርት ነው። ጾም ከምግብና ውሀ ራስን ማራቅ፣ ሰውነትን ማድከም ብቻ አይደለም። አብረውት ሊፈጸሙ የሚገቡ በርካታ ሃይማኖታዊ ትዕዛዞችም አሉት። በመንፈሳዊ ጽድቅን፤ ለአእምሮም እርካታ የሚሆኑ ናቸው። ከሁሉም ግን ‹‹ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት አይሆንም›› የሚል የተለመደ አባባል አለ። ቂምና ጥላቻ ይዞ ጾም፣ በቀልን ይዞ ጸሎት የሃይማኖቶቹ ትዕዛዛት አይደሉምና ከእነዚህ መራቅ ከምግብና ውሀ ከመራቅ በፊት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

ለሁሉም ስህተቶችና ጥፋቶች በቅድሚያ ንሰሐ ያስፈልጋል። ከፈጣሪ መታረቂያው መንገድም ይሄው ነው። ወንድም ከወንድሙ ጋር እየተጋደለ፣ አንዱ አንዱን እያሳደደና እያፈናቀለ ከእህልና ከውሀ በመራቅ ብቻ ድህነትን ማግኘት ይቻላል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። በቅድሚያ ከፈጣሪ ጋር ለመታረቅ ከራስ ጋር መታረቅ ያስፈልጋል። ከተጣሉት ጋር በይቅርታና በምህረት መቀራረብ ይገባል። የተቸገረውን መርዳት፤ ያጠፋውን መውቀስ፤ የተጎዳን መካስ፤ የጎደለውን መሙላት ያስፈልጋል። ይሄ ለመንፈሳዊም ሆነ ለዓለማዊው መንገድ ትልቅ እርካታን የሚያስገኝ ነው።

ይሄ ወቅት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ ትልቁ የአብይ ጾም ነው። የተጣላ ይቅር ተባብሎ፣ ነሰሐ ገብቶ፣ በጾም ጸሎትና ስግደት አምላኩን የሚቀርብበት፤ ሀጢያቱ እንዲሰረይለት አምላኩን የሚማጸንበት ጊዜ ነው። በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድም ረመዳን ትልቁ የእዝነት ወር ነው። የምህረትና ይቅርታ ጊዜ ነው። አማኙ የሚራራበት፣ ያለውን የሚያካፍልበት፤ ከፈጣሪው ምህረትን የሚጠይቅበት ወር ነው። እንግዲህ በእስልምናውም ሆነ በክርስትናው የእምነቱ ተከታዮች ዘንድ የሃይማኖቱን አስተምሮ የሚያሟሉት ይሄንኑ በሙላት ሲፈጽሙ ነው። እያንዳንዳችን ከፈጣሪ ምህረትና ይቅርታን ስንለምን እኛም ከአጠገባችን ላለው ምህረትና ይቅርታን ማድረግ እንዳለብን ሳንዘነጋ መሆን አለበት። እኛ የምንሻውን ከፈጣሪ እንድናገኝ ፈጣሪም ከእኛ የሚፈልገውን ማግኘት አለበት። የእርስ በእርስ ፍቅርን።

ምህረትና ይቅርታ ለነፍስ ድህነትን፣ ለስጋዊ ሕይወትም ሃሴትና የሕሊና እረፍትን ያጎናጽፋል፡፡ ፆም ከምግብ ብቻ ሳይሆን ከክፋት፣ ከቂምና በቀል ራስን ማራቅ ፤ ለምህረትና ይቅርታ ዝቅ ማለት፤ አብሮና ተባብሮ በጋራ መሻገርን የሚጠይቅ ነው። ከፊታችን የሚጠብቀን አገራዊ ምክክርም ይሄንኑ የምህረትና ይቅርታ ልብ ይዞ መነጋገርና መግባባት፣ ተስማምቶ በጋራ መሰለፍን ነው። ለአንድ አገራችን አንድ ሆነን እንድንቆም ነው። አገር ከሌለ እምነት ብሎም ጽድቅ የሚታሰብ አይደለም። አገራችንን በአንድነት ለማቆም ወደምንፈልገው የብልጽግና ማማ ለማድረስ ታዲያ ሰላም ያስፈልጋል።

ሰላም ካለ መከባበሩና መስማማቱ ከሰፈነ ልማቱም እድገቱም አብሮ ይመጣል። ለሁሉም ግን የቆዩ የነበሩ ወይም ያልነበሩ የሀሰት ትርክቶችን አንግቦ ያለፈውን ታሪክ ከመማሪያነት ባለፈ መበቃቀያ በማድረግ አገር ማመስ ዜጎችን መግደልና ማፈናቀል የምናስባትን አገራችንን ለማቆየት የሚያስችል አይደለም። አገር እንደአገር እንድትቀጥል ያለፈውን ጥፋት፤ አሁንም ያለውን አለመግባባት በሰከነ መንፈስ፣ በሆደ ሰፊነት በመነጋገር፣ በመወያየት፣ በይቅርታና በምህረት መተላለፍ ያስፈልጋል።

አገራዊ የምክክር መድረኩ ዋና ዓላማም ይሄንኑ ወደተግባር በመቀየር በአገር ላይ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ነው። አከራካሪና አጨቃጫቂ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ቁጭ ብሎ በመወያየት መፍትሄ ማምጣት ነው። በመሆኑም ይህ የፆም ወቅት ሳይጠናቀቅ የሃይማኖት አባቶች ምዕመኑን ስለ ፍቅር፣ ሰላም፣ ይቅርታና ምህረት ማስተማር አለባቸው። ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ከትምህርትነት ባሻገር በተግባር የሚገለጡ መሆን አለባቸው። አንዱ ለሌላው ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አድርጎ ማሳየት መቻል አለበት።

ምዕመኑም ለእነዚህ መልካም እሴቱ ራሱን ማስገዛት እና ለቀጣዩ አገራዊ ምክክር በንጹህ ልቡና፤ በቅን አእምሮ ለመነጋገር ራሱን ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡ አሁን በአገራችን የሚታዩ የልዩነት አጀንዳዎች የሚጠብቡት፣ ሀሰተኛ ተረኮች የሚታረሙት፣ ለነገም ጠንካራ አንድነት ያላትን አገር መመስረት የምንችለው አጋጣሚው በሰጠን የምክክር መድረክ መጠቀምና ችግሮቻችንን በውይይት መፍታት ስንችል ነው። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ዝግጁ መሆን አለበት። ብሔራዊ የምክክር መድረኩ አገር እንደአገር ለመቀጠል ፍቱን መድኃኒት መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል። ለዚህም ነው ራሳችንን ለምህረትና ይቅርታ ማዘጋጀት ያለብን፡፡


ኢፕድ

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73
ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39
ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ውይይቱ፤ ከምንነቱ እስከ አስፈላጊነቱ

ግርማ መንግሥቴ

በቋንቋ እቅፍ ውስጥ ካሉ ሐረጋት መካከል «እንከን የለሽ» የሚለው አንዱ ነው። እውነትም እንዲህ የሚባል ከሆነ ይህንን ማዕረግ ሊጎናፀፉ ከሚገባቸው ቃላት አንዱና ቀዳሚው «ውይይት» መሆን አለበት። ምክንያቱም «ውይይት» ምንም ዓይነት እንከን ሊወጣለት ስለማይችል። የነጮቹ አፍ በሆነውና የዕለት ተዕለት ቋንቋም «ዲስከሽን» እንበለው፣ አሊያም በፍልስፍናው «ዲያሎግ» በሁለቱም «እንከን የለሽ» ስለ መሆኑ መከራከር የሚቻል አይመስልም። «ይቻላል» ከተባለ እንኳን ሂደቱና ተግባራዊነቱ ላይ እንጂ ጽንሰ ሀሳቡ ላይ ሊሆን የሚችል አይደለም። «ውይይት!!!»

ውይይት በየትኛውም ደረጃ ይካሄድ፤ ምንም ዓይነት እርከን ይበጅለት ውሉም ሆነ አላማው አንድ ነው። አገራዊም ይሁን ብሔራዊ፤ ቡድናዊም ይሁን ቤተሰባዊ ... ውይይት ያው ውይይት እንጂ ክርክር አልያም እሰጥ አገባ ሊሆን አይችልም። ሳት ብሎት ወደ እዚያ ከሄደ እንኳን ችግሩ የእኛ የውይይት አያያዝና አጠቃቀም ጥበባችን (በተለይም የ"Dialogical thinking" /የውይይት እሳቤ) ዝንፈት እንጂ የጽንሰ ሀሳቡ አይደለምና በምንም መልኩ በእሱ ማሳበብ አይቻልም።

ውይይት ምን ጊዜም በዘዴ፣ በጥበብ ከተያዘ፤ በእውቀት ከተመራ ... አዋጭ ነው። በመደማመጥ ላይ ከተመሠረተ፤ በተወያዮች መካከል የጋራ ራእይና አላማ ካለ፣ እራስ ወዳድነትና የአውዳሚነት (ኒሂሊዝም) መንፈስ ከሌለ፣ ማጀቢያው የራስ ፍላጎት ሳይሆን የሕዝብና አገር ጥቅም ከሆነ .... ከሆነ ... ከሆነ ... ምን ጊዜም ውይይት አትራፊ እንጂ አክሳሪ ሆኖ አያውቅም። ከላይ የጠቀስነውን ሩሲያዊ ፈላስፋ ጨምሮ በመስኩ ልሂቃን እንደበት ሲነገር እንደሚሰማው ሕይወት ራሷ (Life is dialogic እንዲሉ) በውይይት የተሞላች ነች እንጂ ተናጠላዊ አይደለችም፤ በመሆኑም ውይይት የሕይወት ቅመም እንጂ መርዝ አይደለም ማለት ነው።

እርግጥ ነው ውይይት ለእኛ ለኢትዮጵያውያን አዲስ አይደለም። ለታክሲ ሳይቀር ስም ስናወጣ እንኳን «ውይይት» ብለን የነበረ ("ነበር" ... ሆነ እንጂ) መሆኑ እራሷ «ውይይት» የተባለችው ታክሲ (አሁንም ድረስ ዘሯ አለና) ምስክር ነችና ጉዳዩ የሚያከራክር አይደለም። «ውይይት»ን በዘፈንም ቢሆን በሚገባ አቀለጻጽሰነዋልና አሁንም ለእኛ አዲስ አለመሆኑ ግልፅ ነው። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አማካኝነት ለንባብ ትበቃ የነበረችው ተወዳጅ ባለ ሁለት ቋንቋ ጆርናልም ስያሜዋ «ውይይት/ዲያሎግ» ነበርና (አይ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እኮ ድሮ ያልቀረ ምን አለ? «ሁሉም ድሮ ቀረ» መባል ካለበት በአንደኛ ደረጃ መባል ያለበት በዚሁ በእናት ዩኒቨርሲቲ ነው።) ስለዚህ ውይይትም፣ መወያየትም፣ ማወያየትም ... ለእኛ ብርቅ አይደለምና እዳው ገብስ ነው ለማለት ነው። ይልቅስ ብርቅ የሚሆነው ስለ «ዲሞክራሲ» ከእኔ በላይ ጠበቃ ሲል የሚሰማው አካል «ውይይት» ሲሉት ሲያቅረውና እግሬ አውጭኝ ሲል ማየት ነውና ጉዳዩ ብዙዎችን ቢያሳስብ አይደንቅም።

በተለይ ወደ ሥነጽሑፍ ሥራዎቻችን ስንመጣ «ውይይት» (ሥነጽሑፋዊ ብያኔው "any communication between two characters" ወይም "the written conversation between two characters or more within a narrative" መሆኑን ልብ ይሏል) ለእኛ አዲስ አለመሆኑን በሚገባ እናረጋግጥበታለን። (ለምሳሌ በፍቅር እስከ መቃብር ውስጥ የተሳኩና ያልተሳኩ ውይይቶችን ልብ ይሏል። (እዚህ ጋ የባክቲን (Mikhail Mikhailovich Bakhtin (1895–1975))ን "Dialogism"ም ማሰብ ይቻላል)፡፡

በውይይት ተጠቃሚ የሆኑ ብዙ አሉ፤ ሰዎች ተጠቅመዋል፤ ቡድኖች ተጠቅመዋል፤ አገራት (ለምሳሌ ጃፓን፣ አልጄሪያ ...) ተጠቅመዋል። መጠቀም ብቻ አይደለም ከገቡበት አዘቅት ሁሉ ወጥተውበታልና ውይይት ፋይዳው ከዚህ መለስ የሚባል አይደለም። ሌላው ሁሉ እንኳን ቢቀር ሩዋንዳዎች ከዚያ ሁሉ ቀውስ ውስጥ አፈትልከው የወጡት (የመሪው ሚና እንዳለ ሆኖ) በውይይትና ግጭት ማስወገጃ ባህላዊ እሴታቸው ነውና ላወቀበት ውይይት ፍቱን መድኃኒት ነው።

ግጭቶች ለምን ኖሩ፣ ተፈጠሩ፣ ተከሰቱ .... ብሎ መከራከሩ ብዙም ፋይዳ የለውም። በተለይ በጥባጭ ባለበት አገር የጠራ ውሀ መጠጣት «ሲያምርህ ይቅር ...» ዓይነት ነውና ግጭት(ቶች) መኖራቸው አይደለም ጉዳዩ፤ ጉዳዩ እንዴት ከግጭቶቹ ወጥቶ ወደ ሰላም መመለስ ይቻላል፣ በምን ዘዴ፣ በምን ብልሀት ... የሚለው ነው አስጨናቂው። ግጭቶች ወደ «የሕልውና ጦርነት»፤ ወደ «የሕግ የበላይነትን የማስከበር እርምጃ» ... ከመሄዳቸውና ምንም የማያውቁ ንፁህን በጅምላም ይሁን በቡድን፣ አልያም በተናጠል ሕይወታቸውን ከማጣታቸውና ቀጥለን የምናስታውሰው ዜና ከመደመጡ በፊት ውይይት ቢቀድም ኖሮ፤ ሁሉም ባልሆነ፣ ዜናውም ሌላ በነበረ ነበር።

«በሕወሓት እና በፌዴራሉ መንግሥት መካከል የተጀመረው ጦርነት እና እሱን ተከትሎ የመጣው ሰብዓዊ ቀውስ፣ የረሃብ አደጋ፣ የንጹሃን ዜጎች ግድያ፣ የሕዳሴ ግድብ ድርድር፣ ከሱዳን ጋር የተገባው የድንበር ይገባኛል ውዝግብ፣ አገራዊ ምርጫ እና ሸኔ የኢትዮጵያ የ2013 ዋና ዋና አጀንዳዎች ነበሩ።» ይላል ይህ በጸሐፊ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ሲያገላብጥ ያገኘው ዜና። ልብ ካልን እነዚህ ሁሉ የውይይት ባህል መንጠፍና የ«በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ውሀ ይጠጣል» ውጤቶች ናቸው እንጂ ሌላ አይደሉም። ወይም እኛ ፈጠሪ ለይቶ እንዲህ እንድንሆን ስላደረገን አይደለም።

ሌላው የዚሁ የ2013 አ.ም ዜናም «በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ሞተዋል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ደግሞ ለረሃብ አደጋ ተጋልጠዋል። በመቶሺዎች የሚቆጠሩ ደግሞ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል። ቁጥራቸው በውል በማይታወቁት ላይ ደግሞ የተለያየ መጠን እና ዓይነት ያላቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተፈጽመዋል።» በማለት (የወደመውን የንብረት መጠን ዘሎታል) ያለፈውን አመት ቀውስ ያብራራዋል። አሁንም እንድገመውና ይህ ሁሉ የውይይት ባህል መንጠፍ እና ለአገርና ሕዝብ ጥቅም ሳይሆን ለግል ጥቅምና ዝና ሲባል የሆነ አሳዛኝ አገራዊ ትራጀዲ ነው።

ለማጠቃለል፣ ባጭሩ ውይይት ማለት ነፍሳቸውን ይማረውና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በአንድ ቆየት ባለ መጽሔት ላይ «ደህና ሁን ጠመንጃ» እንዳሉት ደህና ሁን ጠመንጃ ማለት ነው። ውይይት ማለት ማህበረ-ባህላዊ እሴታችን የሆነው ምርቃታችን «የጎመን ምንቸት ...» እንደሚለው ሁሉ «የሰላም ምንቸት ግባ፤ የግጭት ምንቸት ውጣ» ማለት ነው። ውይይት መደማመጥ ነው፤ ውይይት መነጋገር ነው፤ ውይይት ለጋራ ችግር የጋራ መፍትሄ መሻት ነው፤ ውይይት እነዚህንና እነዚህን መሰል ጉዳዮች ማለት ነውና ለሁሉም መልካም የውይይት መድረክ እንላለን። ችርስ ውይይት!!!

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ



**አ**ቤቱታ የማስተናገጃ ቀን የተለየ ምንም ዓይነት ስብሰባም ሆነ ሌላ ሥራ የማይሠራበት ሲሆን፤ አቤቱታ አቅራቢዎችም በሙሉ በኅብረት አንዱ የሌላውን ችግር እየሰማ እንዲናገሩ እየተደረገ ነው

# ‹‹አንድ መቶ አምስት አቤቱታዎች ቀርበው የመለስንላቸው ከአስር አይበልጡም››

**- አቶ ሞላ ንጉሥ**
**አራዳ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ**

**ምሕረት ሞገስ**

በስፋት ሲነሱ ከነበሩ እና መገናኛ ብዙኃኑን አጨናንቀው ከከረሙ ጉዳዮች መካከል የሕዝብ የውይይት መድረክ ላይ ይነሱ የነበሩ አቤቱታዎች ተጠቃሾች ናቸው:: በሕዝቡ የተነሱ አቤቱታዎችን በማዳመጥ እየተወሰዱ ያሉ ርምጃዎች ካሉ ለመጠየቅ እና አሁንም ድረስ እየቀረቡ ባሉ ቅሬታዎች ዙሪያ ምን እየተሠራ ነው? በማለት አራዳ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሞላ ንጉሥን ጠይቀን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል::

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ በከተማ ደረጃ ከተደረገው ውይይት በተጨማሪ በየክፍለ ከተማው እና በወረዳዎች ውይይት ተካሂዷል:: በዋናነት ተነሱ ብላችሁ የለያችኋቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ሞላ፡-** እርግጥ ነው:: በስምንቱም ወረዳዎች እና በክፍለ ከተማ ደረጃ ውይይቶች ተካሂደዋል:: በውይይቶቹ ላይ የተነሱትን ጉዳዮች ለቅመን ይዘናል:: ወደ ሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች በማከፋፈል በዕቅድ ተይዞ እንዲሠራበት እያደረግን ነው::

**አዲስ ዘመን፡- አገልግሎት አሰጣጥን በሚመለከት ሰፊ አቤቱታ ሲቀርብ ነበር:: ከመታወቂያ ጀምሮ አገልግሎት ለማግኘት ያለው ችግር በዝርዝር ሲገለፅ ሰንብቷል:: ስለሆኑ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጀምሮ በቀረቡ አቤቱታዎች ዙሪያ ምን እየሠራችሁ ነው?**

**አቶ ሞላ፡-** በየመድረኩ የተነሱትን በየዓይነታቸው ለይተናል:: ከሰላም እና ፀጥታ ጋር ተያይዞ የተነሳውን፣ ከአመራር ብልሽት ጋር፤ ብቻ ሁሉንም ለይተን ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር ተወያይተናል:: ጥያቄዎቹ ሊመለሱ የሚችሉት በዕቅድ ነው:: ከክፍሎቹ ጋር በመወያየት በዕቅድ መሠረት መመለስ ተጀምሯል:: በእኛ አካባቢ አንዱ ትልቁ ቅሬታ የሚቀርብበት በልማት የሚነሱ ሰዎችን የተመለከተ ጉዳይ ነው:: ለምሳሌ፣ የሸገር ቁጥር ሁለት የወንዝ ዳርቻ ላይ በሚነሱ ቤቶች ዙሪያ አቤቱታ ይቀርብ ነበር:: ነዋሪዎቹን አስነስቶ በፍጥነት ምትክ አለመስጠት ያጋጥም ነበር:: ስለዚህ መጀመሪያ ያደረግነው ሕጋዊ ሆኖ ቤት ያለውን ሰው ቤት ሳንሰጠው አናነሳም ብለን ወስነናል::

ስለዚህ የቀበሌ ቤት የመረጡ፣ የጋራ መኖሪያ ቤት የመረጡም ሆኑ የግል ቤት ያላቸው ምትክ ቦታ የሚሰጣቸው መሬት ሳይሰጣቸው አይነሱም:: ለምሳሌ 19 ሰዎች የቀበሌ ቤት መርጠው ነበር:: ባለን አቅም 15 ቤት ማቅረብ ችለናል:: ለምሳሌ ሁለት ክፍል ያለው ቤት ከተነሳ መሠጠት ያለበት ሁለት ክፍል ቤት ነው:: ነገር ግን ሁለት ክፍል ተነስቶ አንድ ክፍል ከተገኘ እና ተነሺው ፈቃደኛ ከሆነ ያው ፈቃደኛ በመሆኑ ይሠጠዋል:: ፈቃደኛ ካልሆነ ግን ተመሳሳይ ቤት እስኪገኝለት እንዲለቅ አናስገድደውም:: በዚህ መሠረት ስምንቱ ተረክበው ገብተዋል::

ለእኛ ፈታኝ የሆነው ጥገኛ ነዋሪውን የምናደርገውን ማጣታችን ነው:: እንደሰው ሕፃን ይዘው ማደሪያ ሲያጡ ያሳዝናሉ:: ሕጋዊ እንዳይደረጉ ለሕጋዊዎቹም እጃችን ላይ ቤት የለም:: በዚህ መሠረት የሚቸገሩ ሰዎች አሉ:: የሚያለቅሱ ሰዎች አሉ:: ከሌሎች ዝቅተኛ ነዋሪዎች ጋር ተወዳድረው እንዲስተናገዱ እያረግን ነው:: አንዳንዱን ጥያቄዎች ግን መመለስ አንችልም:: 105 አቤቱታ ቀርቦ የመለስንላቸው ከአስር አይበልጡም:: በተነሳው ጥያቄ ልክ ፈጣን መልስ እየተሰጠ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ከቀረበ፣ መልሳችን መመለስ የማንችላቸው ብዙ ጥያቄዎች አሉ የሚል ነው:: ዋናው ግን የምንችለውን ያለአድሎ ለመፈፀም ጥረት እያደረግን ነው:: ያልተስተናገዱ ሰዎች መኖራቸውን መካድ አንችልም::

**አዲስ ዘመን፡-እነዚህ የተቸገሩ ሰዎችን ለመደገፍ ሌሎች አማራጮች የሉም? ለምሳሌ ቤት የሠሩም ሆኑ ቤት ያገኙ የቀበሌ ቤት ለቀው ሲወጡ በቤቱ ይኖር የነበረ ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ እና ቤተሰብ የመሠረተ በዛ ቤት ኑሮውን መቀጠል እንደሚችል ሰርኩላር ዞሯል:: እየተሠራበትም ነው:: ለእነዚህ የልማት ተነሺዎችስ ለምን ሌሎች አማራጮች ሲገኝላቸው አልቻለም?**

**አቶ ሞላ፡-** በእርግጥ በረዥም ጊዜ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የታሰበው በቤት ግንባታ ላይ የግል ዘርፉን በማሳተፍ ነው:: መንግሥት ቤት እየሠራ ማከፋፈል አይችልም:: ስለዚህ በሽርክና እና በሌሎችም መንገዶች ቤቶችን ለመሥራት የታቀዱ ትልልቅ ዕቅዶች አሉ:: እነዚህ በረዥም ጊዜ የሚሳኩ ናቸው:: አሁን ሊሆን የሚችለው ያለችውን ያለአድሎ ችግር ላለባቸው መስጠት ነው:: እርሷ የምትኖረው ደግሞ ስትለቀቅ ነው:: ወይ ቤት ደርሷቸው እና ሠርተው የሚለቁ ወይም ደግሞ በሕገወጥ የያዙ ሰዎች ካሉ እነርሱን በማስለቀቅ እንሰጣለን:: የቀበሌ ቤት ሲኖር አብሮ የነበረ ቤተሰብ እንዳይለቅ ተብሏል:: አሁን ለወንዝ ዳርቻ የልማት ተነሺዎች ግን ሕጋዊዎቹ ምትክ ይሰጣቸዋል:: ነገር ግን ያስጠጓቸውን ሰዎች ትተው ይሔዳሉ፤ ቀሪዎቹ ደግሞ አቤቱታ ያቀርባሉ:: ቤቱ ደግሞ ይፈርሳል:: ሌላው ግን በተደጋጋሚ የሚቀርቡት አቤቱታዎች የቀበሌ ቤት ይሠጠን የሚል ነው::

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ አበባ ላይ ስር የሰደደ የመኖሪያ ቤት ችግር መኖሩ ይታወቃል:: በዚህ ምክንያት ለሙስና የተጋለጠ ስለመሆኑም ይነገራል:: የሕዝብ ውይይት መድረኮች ላይ በስፋት ቤት እና ሙስናን የተመለከቱ አስተያየቶች ሲሰጡ ነበሩ:: አሠራሩ ከሌብነት የፀዳ እንዲሆን ምን ያህል እየተሠራ ነው? እዚህ ላይ ከቤት ጋር ተያይዞ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ተጨማሪ ክፍያን ማስከፈል የሌለባቸው የዜግነት አገልግሎቶች ሳይቀሩ የሚገኙት በሙስና ስለመሆኑ እና አሁን እንደውም በተደጋጋሚ ይህ እንደሚፈፀም ይታማል:: ስለዚህ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሞላ፡-** ሰጪም ተቀባይም ተጠያቂ ስለሚያደርጋቸው ድርጊቱን የሚፈፅሙት ተደብቀው ነው:: ስለዚህ ማድረግ የምንችለው በአሠራር መከላከል ነው:: ለምሳሌ፣ በጣም ችግረኛ የሆኑ ሰዎች እንዴት ይለዩ ሲባል፤ መለየት የሚጀመረው ከታች ከነዋሪው የሚጀምር ምስክርነት ተሰጥቶበት እና ተለይቶ ሰፊ ውይይት አድርገውበት እና ተስማምተውበት ያስተላልፉሉ:: በነዋሪው የተለየው ደግሞ በወረዳ ካቢኔ ፀድቆ ለክፍለ ከተማ ቤቶች ቀርቦ ይሠጣል:: ይሔ አንደኛው ነው:: ሌላኛው ደግሞ የተለያየ ችግር ያለባቸው ለከተማው ካቢኔ ጥያቄ የሚያቀርቡ አሉ::

ከኃላፊነት ጋር ተያይዞ ወይም የተቸገሩ ሲያጋጥሙ፤ ከከተማ አስተዳደሩ መደበኛ ደብዳቤ ይመጣል:: በዛ መሠረት ይስተናገዳል:: በዚህ መልኩ አሠራር ተከትለን እየሠራን ነው:: በእኛ ክፍለ ከተማ ግን በቀጥታ አጋጥሞን አንድ ሰው እንዲህ ሲቀበል አይተናል የሚል የተረጋገጠ በመረጃ እና በማስረጃ ላይ የተደገፈ ነገር የለም:: ነገር ግን ቅሬታዎች ይነሳሉ:: ለምሳሌ፣ ከእኔ በኋላ ለመጣ ሰው ቤት ተሰጠው የሚል አቤቱታ ይቀርባል:: አንዳንዶች ደግሞ ‹‹ያስወጡን ያለአግባብ ነው›› የሚሉም አሉ:: አሁን አቤቱታ የማስተናገጃ ቀን የተለየ ምንም ዓይነት ስብሰባም ሆነ ሌላ ሥራ የማይሠራበት ሲሆን፤ አቤቱታ አቅራቢዎችም በሙሉ በኅብረት አንዱ የሌላውን ችግር እየሰማ እንዲናገሩ እየተደረገ ነው::

ወረዳ በድሎናል ካሉ እዛው ሁሉም እያየ ፊት ለፊት ስልክ ተደውሎ ሁሉም ሊሰማ በሚችል መልኩ በወረዳ ከሚመለከተው አካል ጋር ውይይት ይካሔዳል:: ጥያቄ ይቀርባል:: እዛው ምላሽ ይሠጣል:: አሁን እልከዋለሁ ባልከው መሠረት ፈጽም ይባላል:: እንዲዚህ እያደረግን ሥራችንን ግልፅ ለማድረግ ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን:: አሁን አንዳንድ ጊዜ አቤቱታ አቅራቢዎች አንድ ላይ ሲናገሩ አንዱ የሌላውን ችግር አይቶ የኔ በሌላ ጊዜ ይደርሳል እስከማለት የሚደርሱበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: አንዱ ተጨናንቀናል ሌላ ቀይሩልን ሲል አንደኛው

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

የምንኖረው ሽራ በተወጠረ ቤት ነው የሚል ሲያጋጥም የምንኖረው ተጨናንቀን ነው የሚለው ሰው ጥያቄውን ባይተወውም ይዘግይ ብሎ ትቶ ይሔዳል::

በተቻለ መጠን የአሠራር ብልሹነትን ለመከላከል መጀመሪያ አሠራርን ማየት ያስፈልጋል:: እኛ አሁን ላይ አቤቱታ ሲቀርብ የምንሰማው ሁላችንም ነን:: ያለምንም መደባበቅ እኔ ብቻ ሳልሆን ምክትሉ እና አማካሪዎች እንዲሁም ሌሎች አቤቱታ አቅራቢዎች እየሰሙ ፊት ለፊት ይቀርባል:: በተቻለ መጠን አሳታፊ ለማድረግ ጥረት እያረግን ነው:: ነገር ግን የሁሉንም አካላት ተሳትፎ ይጠይቃል:: ሕዝብን ማንቃት ይገባል::

**አዲስ ዘመን፡- ከመኖሪያ ቤት በተጨማሪ የመሥሪያ እና የመሸጫ ሼዶች ፍትሐዊ ክፍፍልን በሚመለከት ተደጋጋሚ ሮሮዎች ይደመጣል:: ለምሳሌ አንድ ሰው ሶስት እና አራት ሼድ ሲኖረው ሌላ መሥራት የሚችል ነገር ግን የመሸጫም ሆነ የመሥሪያ ቦታን መከራዬት የማይችል ሰው አንድም ሳያገኝ የሚቀርበት ሁኔታ አለ:: ይህንን በተመለከተ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሞላ፡-** ትክክል ነው:: በሕዝብ መድረኩ ላይ ከተነሱ ጉዳዮች መካከል ሀብት ያፈሩ ከአምስት ዓመት በላይ የሆናቸው አሁንም ድረስ ሼዶችን የያዙት ለምን አይለቁም የሚል አቤቱታ ቀርቧል:: ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ምን ያህል ሰው መቼ ሼዶችን ወሰደ ምን ያህል ሃብት ፈጠረ የሚለውን እያጠናን ነው:: በሌላ በኩል አሁን የሠራናቸው ትንንሽ ሱቆች አሉ:: እነሱ ላይም እንደባለፈው ዓይነት ስህተት እንዳይሠራ በተቻለ መጠን በትክክል ለሚገባው ሰው እንዲደርስ ልክ የቀበሌ ቤት ላይ እንደተሠራው አሁንም ከማኅበረሰቡ እንዲመጣ እየተሠራ ነው:: ነገር ግን ራሱ ሰው መተሳሰብ አለበት:: ሃብት ከፈጠረ ለሌላው ሰው መልቀቅ ሲኖርበት ይዞ ከቆየ ከባድ ነው:: አሁን ቀድሞ ያዩዙት ልቀቁ ሲባሉ እነርሱ ራሳቸው አልቃሽ ይሆናል:: እነርሱ ራሳቸው የቅሬታ አቅራቢዎች ይሆናሉ:: እውነት ነው ይሔ ሕዝብ የሚያነሳው ጥያቄ መፈታት አለበት:: ነገር ግን ሁሉም ማሰብ መረዳት እና መተጋገዝ አለበት::

**አዲስ ዘመን፡- በአገሪቷ በነበረው ጦርነት፣ በዓለም ደረጃ ባጋጠመው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ፤ እንዲሁም በተከሰተው የዓለም የፖለቲካ ቀውስ እና በሌሎችም በተለያዩ ምክንያቶች የኑሮ ውድነቱ ማኅበረሰቡን እያንገላታው ነው:: ይህም የሕዝብ መድረኩ ላይ በዋነኛነት ትልቅ አቤቱታ ሆኖ ሲቀርብ ነበር:: በእናንተ በኩል ምን እየሠራችሁ ነው?**

**አቶ ሞላ፡-** የኑሮ ውድነቱን ችግር ለማቃለል ዋነኛው ዘላቂ መፍትሔ አቅርቦቱን መጨመር ነው:: በእርሱ ላይ በአገር ደረጃ ምርት መጨመር ላይ የሚሠራ ይሆናል:: ነገር ግን አሁን ላይ በክፍለ ከተማው ሰው ሰራሽ ችግርን ለመፍታት ጥረት እያደረግን ነው:: ይሔ በስግብግብነት የሚፈጠረውን ችግር ለማቃለል ቤት ለቤት አሠሣ በማድረግ በአንድ ወር ውስጥ ወደ ስምንት ሺህ የንግድ ሱቆች ተፈትሸው 264ቱ ላይ ያለአግባብ ለገበያ መዋል ያለበትን ምርት አከማችተው ተገኝተዋል:: አንድ ሺህ 511 ሊትር ዘይት፣ 15 ኩንታል ስኳር ተገኝቷል:: ስለዚህ አንዱ ሰውሰራሽ እጥረትን ለመቀነስ ሠርተናል:: በተጨማሪ ስኳርና ዘይት ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ምርቶችን የሚያቀርቡ በክፍለ ከተማው ባሉ 10 የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበር በ56 ሱቆች የተለያዩ ምርቶች እየቀረቡ ነው:: እዚህ ላይ ምርት ቶሎ እንዲሠራጭ ማድረግ ነው:: ሸማቾች ጋር የገቡ ምርቶች ቶሎ ኅብረተሰቡም ሆነ ሱቆች ጋር በፍጥነት እንዲደርሱ ማድረግ ተችሏል:: በአካል በመሔድ ሱቆችን ለማየት ሞክረናል::

አሁን ወደ ሱቆች ስንሔድ ስኳር ብዙ ችግር አይደለም፤ በቅርብ ይገኛል:: ሙሉ ለሙሉ ችግሩ ተቀርፏል ባይባልም፤ ይሻላል ብሎ መውሰድ ይቻላል:: ሁለተኛ የከተማ አስተዳደሩ ወደ 100 ቢሊዮን ብር ለሸማቾች ድጎማ አድርጓል:: ይህ ተዘዋዋሪ ገንዘብ ነው:: እኛ ወደ 100 ሚሊዮን አግኝተናል:: ይሔ ጤፍ እና ስንዴ ብቻ የሚገዛበት ነው:: ሸማቾች ከአርሶ አደሩ በቀጥታ አምጥተው እንዲያስቀምጡ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው:: በዚህ መሠረት በ87 ሚሊዮን ብሩ እህል ገዝተንበታል:: በዚህ መሠረት ነጭ ጤፍ 7ሺህ 751 ኩንታል፤ ሰርገኛ 7ሺ 67 ኩንታል ገዝተናል:: ቀይ ጤፍም 2ሺህ አንድ መቶ ኩንታል ገዝተናል::

የዋጋ ልዩነቱ ነጭ ጤፍ ከእኛ የሸማቾች ማኅበራት 4 ሺህ 750 ሲሸጥ፤ ውጪ ግን 5 ሺህ 300 ብር እየተሸጠ ነው:: ሰርገኛም 4ሺ 300ብር ሲሆን፣ ውጪ 4ሺህ 600 ብር እየተሸጠ ነው:: ቀይ ጤፍም ተመሳሳይ ልዩነት አለው::



**ምን ያህል ሰው መቼ ሼዶችን ወሰደ ምን ያህል ሃብት ፈጠረ የሚለውን እያጠናን ነው**

ስለዚህ በትንሹ የአራት መቶ እና የሶስት መቶ ብር ልዩነት አለ:: ነገር ግን ይህ ሁሉ ሲታይ በቂ እና እርካታን የፈጠረ ነው ማለት አይደለም:: ነገር ግን ለመሥራት እየተሞከረ ነው::

እሁድ ገበያም በክፍለ ከተማችን በሁለት ቦታዎች ላይ የአርሶ አደር እና የፋብሪካ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ጥረት እየተደረገ ነው:: እስከ አሁን ወደ 9 ነጥብ 6 ሚሊዮን ብር የተለያዩ ዓይነት ምርቶች ሽያጭ ተካሂዷል:: እስከ አሁን ስድስት ኪሎ እና ጊዮርጊስ አካባቢ ባለው ሽያጭ ብቻ ሲሆን፤ አሁን ደግሞ በተጨማሪነት ሾላ አካባቢም እየተጀመረ ነው:: ዝም አልተባለም ችግሩን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- በክፍለ ከተማው እየተስተዋለ ያለውን እና በተደጋጋሚ እየተጠቀሰ የሚገኘውን የፀጥታ ችግር በሚመለከትስ ምን እየተሠራ ነው? ሰሞኑንም ተባብሶ ስለመቀጠሉ ይነገራል:: በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሞላ፡-** ከፀጥታ ሁኔታ ጋር ተያይዞ ስንጠቁም ቶሎ አይደርሱልንም የሚል ከኅብረተሰቡ በፀጥታ ኃይሉ ላይ አቤቱታ ቀርቧል:: ከላይ እንደተገለፀው በእነርሱ በኩልም የቀረቡባቸውን አቤቱታዎች ቆጥሮ በመግለፅ አውቀው እንዲሠሩበት አቅጣጫ ተቀምጦላቸዋል:: በፊት የሕልውና ዘመቻ ጦርነት በነበረበት ጊዜ የፀጥታ ኃይሉም ሆነ ኅብረተሰቡ ጥበቃውን በብሎክ ሳይቀር አጠናክሮ ነበር:: አሁን ግን የተወሰነ መላላት አለ:: ይህንን ችግር ለመፍታት ማኅበረሰቡም ጥበቃውን እንዲያጠናክር፤ የፀጥታ ኃይሉም ጥያቄ ሲቀርብለት ቶሎ የሚደርስበት ሁኔታ እንዲፈጠር እየሠራን ነው::

**አዲስ ዘመን፡- የመሬት ወረራ ላይ ሰፊ ችግር እየተስተዋለ ስለመሆኑ ይነገራል:: ከዚህ ጋር ተያይዞ እናንተ ጋር ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን እየሠራችሁ ነው?**

**አቶ ሞላ፡-** በሌሎች ክፍለ ከተሞች ላይ እንዳለው የተጋነነ ባይሆንም አሁንም በተለይ በወንዞች ዳርቻ አካባቢ እኛ ክፍለ ከተማ ላይም የመሬት ወረራ ችግሮች አሉ:: አንዱ የምናፈርሰው ሕገወጥ የሆነው በወንዞች አካባቢ የሚስተዋለው ነው:: ከ20 በላይ ቤቶችን አፍርሰናል:: ተቸግረው መሥራታቸውን ቢገልፁም ሕገወጥነት መስፋፋት ስለሌለበት እያፈረስን ነው:: በየቦታው ሸራ ወጥረውም የሚሠሩ እና የሚኖሩ አሉ:: ለምሳሌ ቴድሮስ አደባባይ አካባቢ አፍንጮ በር አካባቢም ሸራ ወጥረው የሚኖሩ አሉ:: እርሱን ችግር ለመፍታት እንሠራለን::

**አዲስ ዘመን፡- መሬት ነክ ጉዳዮች በክፍለ ከተሞች ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ለምን ይቀርባሉ? ቤት ከሌለ ቤት የለም ተብሎ በግልፅ የማሳወቅ ሥራ ለምን አይሠራም:: ለምን ችግሮች እንዲፈቱ የከተማው አስተዳደር ድረስ ጥያቄያችሁን አትዘልቁም? በኢኮኖሚ በኩል ያለውንስ?**

**አቶ ሞላ፡-** ሁሉም ነገር የመጣው ሁሉ በአንዴ እንደማይፈታ ኅብረተሰቡም ያውቃል :: የሚያስፈልገው በቅርብ ጊዜ የሚሆነውን ይሆናል:: በቅርብ ጊዜ የማይሆነውን አይሆንም በማለት ምላሽ እየሰጠን ነው :: አሁን እያደረግን ያለነው እሱን ነው። አሁን የተነሳውን የቤት ችግር እናንሳ የጋራ መኖሪያ ቤት እንሰጣለን ተብሎ በ1997 ተጀምሮ ነበር :: ነገር ግን ተመዝጋቢዎቹ ምላሽ ሳያገኙ በ2005 ሌላ ምዝገባ ተካሔደ:: በዚያ ዓመት የተመዘገበው በጣም ግዙፍ ቁጥር ነው :: እሱ ገና አልተነካም :: ስለዚህ የቤት ችግር ውስብሰብ እና ሰፊ ነው:: ይህን ችግር ሺህ አመት ብንቆይ እንኳ በዚህ አካሔድ አንፈታውም :: ስለዚህ እንዲህ አይነቱ ችግር የአሰራር ለውጥ ያስፈልገዋል:: በመሆኑን በብዛት ይህን ችግር ለመቅረፍ የግል ባለሃብቱን ለማሳተፍ እየተሠራ ነው:: መታወቅ ያለበት ግን ዝም ብሎ ችግሮችን መስማት ብቻ ሳይሆን አማራጮችን ማሰብ ያስፈልጋል::

አሁን እየተነሳ ያለው የኑሮ ውድነትም ቢሆን መፍትሔው አገራዊ ምርቱን መጨመር ነው:: ለምሳሌ ከውጪ ከምናመጣቸው ነገሮች አንዱ ስንዴ ነው:: ስለሆነም በሚቀጥሉት ሁለት አመታት ከውጭ የምናመጣውን ስንዴ ማቆም አለብን ተብሎ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው :: ለኢኮኖሚ ችግሮች በቂ ምላሽ መስጠት ያልተቻለው ፍላጎት እና አቅርቦቱ ባለመመጣጠኑ ነው :: እንደዚህ አይነቱን ችግር ለመቅረፍ ደግሞ መነጋገር እና መግባባት ያስፈልጋል::

**አዲስ ዘመን፡- ጊዜዎትን ሰጥተው ለቃለ ምልልሱ ስለተባበሩኝ አመሰግናለሁ!**

**አቶ ሞላ፡-** እኔም አመሰግናለሁ!

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## "የአጉራ ዘለል [ጀግንነት;] መገለጫዎች!"

**መንደርደሪያ ቢሆነን...፤**

የዛሬው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ የቀድሞው ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ፤ ከ1954 ዓ.ም በኋላ ደግሞ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርስቲ በመባል የሚታወቀው የአገሪቱ ታላቅና አንጋፋ የትምህርት ተቋም በየዓመቱ ተወዶና ተናፍቆ የሚጠበቅ የኮሌጅ ቀን የሚባል ዓመታዊ የተማሪዎች በዓል ነበረው:: በዚህ በዓል ላይ በከፍተኛ የክብር እንግድነት የሚገኙት ንጉሠ ነገሥቱ ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ነበሩ:: ንጉሡ በበዓሉ ላይ ሲገኙ በተለይም በግጥም ውድድር አሸናፊ የሚሆኑትን "ተማሪ ልጆቻቸውን" (ቀኃሥ፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን የሚጠሩት ልጆቻችን እያሉ መሆኑን ልብ ይሏል) የሚሸልሙትና የሚያበረታቱት በታላቅ የደስታ ስሜት እንደነበር የዘመኑ ታሪክ ማስረጃችን ነው::

እየዋለ እያደረ ግን በበዓሉ ላይ የሚቀርቡት አብዛኞቹ ግጥሞች ንጉሠ ነገሥታዊውን ሥርዓት፣ ሥር ሰዶ የኖረውን ፊውዳላዊ ፖለቲካና ንጉሡን ራሳቸውን ሳይቀር ግልጥልጥ አድርገው ይተቹና ይሄሱ ስለነበር መዳፈሩ እየጠነከረ በመሄዱ ንጉሡ በበዓሉ ላይ ላለመገኘት እርም ብለው ሊቀሩ ግድ ሆኗል::

በ1951 ዓ.ም በተከበረውና ንጉሡ በታደሙበት በዓል ላይ ተገኝ የተሻወርቅ የተባለ ተማሪ "ሰው ዕንቆቅልሽ ነው" የሚል ግጥም አቅርቦ ንጉሡ ከመደሰታቸው የተነሳ ትምህርት ሚኒስቴር መ/ቤት ግጥሙን አባዝቶ ለአገሪቱ ተማሪዎች በሙሉ እንዲሠራጭ እስከ ማዘዝ ተደርሶ ነበር:: ዘለግ ያለውና ንጉሡን "ከዙፋን አስነስቶ ያስጨበጨበው"፤ [ማስጨብጨቡና ከዙፋን ላይ የመነሳቱ ገለጻ ሥነ ጽሑፋዊ ውበት ለማከል ታስቦ መሆኑ ይሰመርበት]፤ ሙሉው ግጥም በዚህ ገጸ-ዘመን ላይ እንዳይታተም ዐውዱም ሆነ የጋዜጣው የዓርብ ውሱንነት ስለማይፈቅድ ስድስት ያህል ስንኞችን መርጠን በማውጣት ለማሳያነት እንገለገልበታልን፤ ወዲያውም ለመንደርደሪያ እንዲያግዘን ጭምር::

**"ንገሩን እናንተ ገባን የምትሉ፣**
**ይሄ ነው ብላችሁ የአገር ልጅ ባህሉ::**
**ክፋቱን ጥፋቱን ባንድ ፊት አርጉና፣**
**ልማት ደግነቱን ወደዚህ ለዩና፣**
**አንፍሱ አንንጓሱና ብጥር አድርጋችሁ፣**
**ንገሩኝ [የአገር] ልጅ ይሄ ነው ብላችሁ::**

ከዚህ በላይ ተቆንጥረው የተጠቀሱት ጥቂት ስንኞች ለዚህ ጽሑፍና ለጊዜያችን ዐውድ መንደርደሪያነት የተሻለ መልዕክት ያስተላልፋሉ ተብሎ በመታሰቡ እንጂ ሙሉ ግጥሙ በራሱ የያዘው እምቅና ሞጋች መልእክት በስፋት ቢተነተን ብዙ እንማርበት ነበር::

**"እፍረተ ቢሱ" ዘመናችን፤**

በግጥሙ ውስጥ እንደተጠቀሰው ሁሉ ይህ የእኛ ዘመንም በዕንቆቅልሽ በተተበተቡ በርካታ ክስተቶች የተሞላ ነው:: በጎነቱንና ክፋቱን አንፍሰንም ሆነ አንጓለን ውጤቱ ይህን ይመስላል ለማለት አቅምም፣ ዕድልም አሳጥቶ ያሽመደመደን ይመስላል:: ያለምንም ማመንታት ደፈር ብለን ለመወያየት ወኔያችን ለማኮስተር ከፈቀድን ጊዜያችን ሰልጥኖብን አስገብሮን ካልሆነ በስተቀር ጊዜውን ለመዋጀት አቅም እንዳነሰን መገንዘቡ አይገድም:: ጊዜው ይበራል፤ ይከንፋል:: አብረን ለመክነፍና ለመብረር ክንፍም ሆነ ጥበብ የራቀብን ይመስላል:: ተወዳጁ መምህራችን ደበበ ሰይፉ በገጣሚነት ምናቡ ጊዜን የገለጠበት ምልከታ ለጥጠን ለነካካነው ሃሳብ ጥሩ

**"አጉራ ዘለልነት"፡ - ስድ አደግነት፣ ባለጌነት፣ ጋጥወጥነትና ሥርዓት አልበኝነትን እንዲገልጽ ሆኖ ትርጉሙን አስፍቷል:: ይህን መሰሉ አጉራ ዘለልነት ከማፈሪያነትና አሸማቃቂነት ነፃ ወጥቶ ተግባሩን የሚፈጽሙት ዜጎች ልክ እንደ "ጀግናና ቁምነገር ፈጻሚ ባለውለታዎች" በሆታና "በዕልልታ" እየደመቁ ሲበረታቱ ማስተዋልና ተከታዮች ሲያበዙ መመልከት ከአሳፋሪነቱ ይልቅ እንደ "ክብር" ተቆጥሯል:: ቅዱስ መጽሐፍ "ነውራቸው ክብራቸው" እንደሚለው መሆኑ ነው**

መሰብሰቢያ ስለመሰለን እዚህ ስፍራ እናስታውሰዋለን::

**ጊዜ በረርክ በረርክ፣**
**ጊዜ በረርክ በረርክ፣**
**ግና ምን አተረፍክ?**
**ግና ምን አጎደልክ?**
**ሞትን አሳሸነፍክ፣**
**ሕይወትን አልገደልክ::**

እውነት ነው፤ ጊዜ ይበራል ይከንፋል:: ለአብነት ያህል ከጋራ ጉዳዮቻችን እንምዘዝና ጊዜው እየተገዳደረን ከእጃችን ላይ ያስጣለንን ጥቂት ማሳያዎችን እናመላክት:: በየብሔረሰቡ "ነዎሩ" ሲሰኙ የኖሩት የሰው ለሰው መስተጋብር ባህሎች፣ በእድሜ የከበሩ ወግና ልማዶች፣ ተፈጥሮ የሚያስተምርንና በህሊና የምንዳኝባቸው በጎ ተግባራትና ድርጊቶች አደጋ ላይ እየወደቁ ግራ በመጋባት አመሳቅለውናል:: መልካም የሚሰኙ ማሕበራዊ እሴቶቻችንም ከእጅ ወድቆ እንክትክት እንደሚል ብርጭቆ በፊታችን ዕለት በዕለት ሲሰባበሩና ሲፈረካከሱ እያስተዋልን ነው::

እጅግ የሚገርመው ተቃርኖ ደግሞ ይሄው ኅብረተሰባዊ ስብራታችን እንደ "ጀግንነት" መቆጠሩ ነው:: በርእሱ ላይ በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ የተቀነበበው "ጀግንነት" በበጎና በአርአያ ገላጭነት ተግባሩ ወካይነት የሚጠቀስ ሳይሆን ለምጸታዊ ገለጻና ማሳያ የቀረበ መሆኑን ማስታወሻ በማኖር ወደ ዝርዝሩ እንዝለቅ:: ለምሳሌ፡- በርካታ ዜጎች በተለያዩ ማኅበራዊ ሚዲያዎችና የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ፊት ለፊት ብቅ እያሉ ወይንም በቴክኖሎጂ መጋረጃዎች ተጋርደውና አሸምቀው፤ ሲያሻቸው በራሳቸው ማንነት፣ ሲፈልጉም ስምና ፎቶግራፋቸውን በግላጭ እያስተዋወቁ አጉራ ዘለልነታቸውን ሲገልጹ "መብታቸው እስኪመስላቸው" ድረስ በልበ ሙሉነትና በድፍረት ነው::

ሥነ ምግባር ይሉትን የኅብረተሰብ ኬላ እየጣሱ መሳደብና የፈለጉትን ሰው እስከ ማዋረድ መድረስ የተለመደ ክስተት ከሆነ ውሎ አድሯል:: መለመዱም እንደ "ጀግነንት" እየተቆጠረ በተመሳሳይ ቢጤዎቻቸው ለአጉራ ዘላዮቹ ድርጊት በአደባባይ ይጨበጨብላቸዋል:: አድናቆቱም በፉጨት ታጅቦ ይዥጎደጎድላቸዋል:: "ከሰደበኝ መልሶ የነገረኝ ገደለኝ" እንዲሉም ስድቡ እንደ ወዳጅ የግብዣ ጥሪ አድራሻቸው፣ አካውንታቸው፣ የፌስ ቡክ ገጻቸው፣ ቲዩተራቸው፣ ኢንስታግራማቸው ወዘተ. እየታሰሰ እንዲደርሳቸው ይደረጋል::

ስለ አጉራ ዘለልነት ካነሳን ዘንድ ጥቂት ማብራሪያ ያስፈልግ ይመስለናል:: ሕጋዊ ፍቺ ሳትፈጽም በቅብጠትም ይሁን በክህደት ከባሏ ቤት ጠፍታ የኮበለለችን ሴት ወይንም ሚስቱን የከዳ ወንድን ባህላችን የሚበይናቸው "አጉራ ዘለል" በማለት ነው:: የፈሊጡ ፍቺ እየሰፋ ሄዶም "አጉራ ዘለልነት"፡- ስድ አደግነት፣ ባለጌነት፣ ጋጥወጥነትና ሥርዓት አልበኝነትን እንዲገልጽ ሆኖ ትርጉሙን አስፍቷል:: ይህን መሰሉ አጉራ ዘለልነት ከማፈሪያነትና አሸማቃቂነት ነፃ ወጥቶ ተግባሩን የሚፈጽሙት ዜጎች ልክ እንደ "ጀግናና ቁምነገር ፈጻሚ ባለውለታዎች" በሆታና "በዕልልታ" እየደመቁ ሲበረታቱ ማስተዋልና ተከታዮች ሲያበዙ መመልከት ከአሳፋሪነቱ ይልቅ እንደ "ክብር" ተቆጥሯል:: ቅዱስ መጽሐፍ "ነውራቸው ክብራቸው" እንደሚለው መሆኑ ነው::

"ላም እሳት ወለደች፤ እንዳትልሰው ፈጃት እንዳትተወው ልጅ ሆነባት" እንዲል አገራዊ ብሂላችን፤ የዘመናችን ሳይንስና ቴክኖሎጂ ያጎናጸፈን የማኅበራዊ ሚዲያው "በረከተ መርገም" ለብዙ አጉራ ዘለሎች የመፈንጫ ነፃ መድረክ እንደሆነ እስኪያቅረንና እስኪያጥወለውለን ድረስ ሳንወድ በግድ ለመጋት ተገደናል::

በመግቢያው ላይ በተጠቀሰው የንጉሡ ዘመን እንደ ከዋክብት ደምቀው ከነበሩት የዚያ ትውልድ አባላት መካከል ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ (ገሞራው) በ1959 ዓ.ም ለዚያው የኮሌጅ ቀን በዓል ያቀረበውን አንድ የግጥም ሥራውን በዚህ ቦታ ማስታወስ ግድ ይላል:: ሳይንስና ቴክኖሎጂው የወለዳቸው መልካም ነገሮች ለግፍና ለበቀል ማወራረጃነት ሲውሉ የተመለከተው ገሞራው፤ "በረከተ መርገም" በሚል ርዕስ እንደ ገሞራ እሳት በሚፋጀው ብዕሩ አንድ ዘለግ ያለ ዘመን አይሽሬ ግጥም ጽፎ ነበር:: ይህ ግጥም ስሜቱን የኮረኮረው የዘመናችን ገጣሚ በዕውቀቱ ስዩም "በረከተ መርገም ቁጥር 2" በሚል ርዕስ መሰል ይዘት ያለውን ትዝብቱን በተባ ብዕሩ የገለጠው እንዲህ በማለት ነው::

ኮምፒውተር የሚሏት የደብተራ ሳጥን ከመጣች ጀምሮ፣

**በወግ መኖር ቀረ አስማት ሆነ ኑሮ::**
**ከተፈጥሮ ሸሸ ሰው ከሰው መነነ፣**
**መኖርና መሞት ክሊክ ማድረግ ሆነ::**
**ወንበር ላይ ተጥዶ ወንበር ላይ እንዲያረጅ፣**
**ትውልዱ ላይ አዚም የጣልክበት ፈረንጅ፣**
**የፌስቡክ ፈብራኪው ጎረምሳው ዲታ ሰው፣**
**የግፍ ንብረትህን በልተህ ሳትጨርሰው፣**
**የየካው ሚካኤል ዐይንህን ያፍስሰው::**
**አቤት ተቀምጩ ባለ ሥልጣን ሳማ፣**
**ቤቱ ተቀምጦ አጅሬ እንዲሰማ፣**
**በጅ የማይዳሰስ የሃሜት ሰንሰለት የዘረጋህለት፣**
**ሞባይል ፈጣሪው የቴሌፎን ጌታ፣**
**በኖርክበት ዘመን ባለህበት ቦታ፣**
**አቡነ አረጋዊ ይጣሉህ በቴስታ::**

በመምህሩ ይቀጣ እንደ ነበር የቀድሞ ታዳጊ ተማሪ ይህ ዘመን በእንብርክክ እያስኬደንና እየቀጣን "አጉራህ ጠናን" (ተሸነፍን፣ ተረታን እንዲሉ) ብዙ ዜጎች የአጉራ ዘለሎቹን ተግባር በአሜንታ በመቀበል፤ አንድም፡ - "ዘመኑ ነው መቼስ ምን ይደረጋል" በሚል ቁጭት እየተብሰለሰሉ፤ ሁለትም፡- እንደ "እብድ ገላጋይ" መልሰው እሳትና ጭድ ጎን ለጎን እያቀባበሉ የአለሌዎችን ስድቦች ሲያራግቡና ሲያቀጣጥሉ መመልከት እፍረትንም ሆነ አሸማቃቂነት ወደ ጎን በመግፋት ነው::

ከፍታና ዝቅታ፣ ሥልጣነ ክህነትና ሥልጣነ ፖለቲካ ሞገሳቸው ተገፎ በስድብ ሲገረፉ መዋል የዕለት ክስተት፣ በየደቂቃው የሚፈጸም "የጀግኖች ድርጊት" ሆኖ ሥር ከሰደደ ሰንብቷል:: ለታላላቆችና ለአንቱዎች የሚሰጠው ክብርም እንዲሁ ታሪክ ሆኖ በነበር ሊዘከር የቀረው አንድ ሐሙስ ብቻ ነው::

በዚህ ዘመን ወለድ የቴክኖሎጂ ዘመን ያበዱትና የሚያሳብዱን በአንድ የዕድሜ ክልል ውስጥ የተጠለሉ ዜጎች ብቻ አይደሉም:: ከሕጻናት እስከ ታዳጊዎች፣ ከወጣት እስከ ባለሽበቶች፣ በመንበረ ሥልጣን ላይ ከተቀመጠ ቁንጮ መሪ እስከ የቤተ እምነት አውራ መሪ፣ ከካህን እስከ መምህር፣ ከአዋቂ እስከ ተደናቂ፣ ከማጀት እስከ ፍርድ አደባባይ በዋልጌዎች ያልተለከፈ፣ ለአጉራ ዘለልነት ገብሮ ከማኅበራዊ ባህሎቻችን ያልተፋታ ዜጋ በወረንጦ እንኳን ቢታሰስ የሚይገኝበት ጊዜ ፈጥኖ እንዳይደርስብን ከፍ ያለ ስጋት ላይ ጥሎናል:: በአጭሩ፡ - "የዘመነ ነፃነቱ ባሪያ ሆኖ የዋልጌነት ዛር ያልሰፈረበት" ዜጋ ማግኘት አዳጋች ሆኗል እስከ ማለት እንዳንደፍር ያሰጋል::

ተሳዳቢነት እንደ ጀግንነት፣ ተዋርዶ ማዋረድ እንደ ኒሻን ተሸላሚ አስቆጥሮ በአድናቆት ሲጨበጨብ ከማስተዋል ውጭ ምን ምስክር መጥራት ይቻላል:: ሃይማኖት ተንቆ ርኩሰት የገነነበት፣ ቀኖና ተሸሮ የሕሊና ዐይን የታወረበት ይህ ዘመን ተዋርዶ አዋርዶናል:: እርስ በእርስ መዘነጣጠላችን እንደ ወግ ተቆጥሮ ድጋፍ ይሰበሰብበታል፤ ቅንጥብጣቢ የዩቲዩብና "የሼር" ያልተቀደሰ ሀብት ይጋበስበታል:: በርግጡ ይህ "ሰድቦ ለሰዳቢ" አሳልፎ ለመስጠት ትውልዱን ያጀገነው ዘመን የት ደርሶ ምን ላይ ይጥለን ይሆን? ርዕሰ ጉዳዩን ዳግም ጫን ብለን ለማብላላት እንመለስበታልን:: ሰላም ይሁን::

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# በሀዋሳ ከተማ የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በአሁን ወቅት ነዋሪዎች በአንድ ልብ አንድ ቃል ከተናገሩ ስለ ኑሮ ውድነት ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም:: በተለይም በምግብ ሸቀጦች ላይ ዕለት ተዕለት እየታየ ያለው የዋጋ መናር ማኅበረሰቡ ከሚችለው አቅም በላይ እንደሆነበት ምስክር መጥራት አያሻም :: ማንኛውም መገበያያ ሥፍራ የሚደመጠው እያንዳንዱ የፋብሪካም ሆነ የግብርና ምርት ጨመረ እንጂ ቀነሰ አይደለም። ቀልድ ቁምነገሩ ፣ፌዝ ተረቱ ሁሉ ይሄንኑ የሚጠቁም ነው ::

እርግጥ ነው ኅብረተሰቡ በእጅጉ የተማረረበትን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት በሚል መንግሥት በተለያየ ጊዜ የወሰዳቸው እርምጃዎች ቢኖሩም ችግሩ ግን ሊቃለል አልቻለም:: የኑሮ ውድነቱ ከከተሞች ባለፈም በገጠርና በገጠር ከተሞች ጭምር ዜጎችን እየፈተነ ያለ ለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ:: ተባብሶ የቀጠለው የኑሮ ውድነት ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ባሉ የክልል ከተሞች ጭምር ጫናው የበረታ ነው ::

የዝግጅት ክፍላችንም በሀዋሳ ከተማ ያለው የገበያ ሁኔታ እንዲሁ አገራዊ የሆነውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት ምን ምን ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ መመልከት ችሏል:: በከተማው ነዋሪ ከሆኑት መካከል ወይዘሮ ቦንሳ ታዲዎስ እና አቶ አርጋው በሰጡን አስተያየት የኑሮ ውድነቱ ከዕለት ዕለት እየተባባሰ ነው። በተለይ እንደ ዘይት አይነቱ ደግሞ ዋጋው ከመጨመሩም በላይ በገበያ ላይ እንደልብ አይገኝም። አሁን አንዳንድ ምርቶች ትንሽ ቅናሽ ያላቸው የሸማቶች ኅብረት ስራ ማኅበራት የሚያቀርቡት ነው። ዱቄት በሱቅ ውስጥ ከሚሸጠው በተሻለ በድንኳን ውስጥ የስምንት ብር ቅናሽ አለ ። እንዲሁም ሙዝ ዋጋው በኪሎ እስከ 40 ብር ደርሶ ነበር አሁን ግን የመቀነስ አዝማሚያ አለ ። ይሁን እንጂ አሁንም የኑሮ ውድነቱን መቋቋም አቅቶናል መንግሥት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በከተማው የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት የተሠሩ ሥራዎች መኖራቸውን የገለጹት ደግሞ በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር የኅብረት ሥራ ልማት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጴጥሮስ ዮሐንስ ናቸው::

እንደሳቸው ማብራሪያ የኑሮ ውድነቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተባባሰ የመጣ እንደሆነና ለዚህም በዋናነት የሚጠቀሱ ሁለት ምክንያቶች እንደሆኑ ነው:: በቀዳሚነት ያነሱት እንደ ሀዋሳ ከተማ በግብርና ምርቶች እንዲሁም በኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ ሰፊ የሆነ የአቅርቦት እጥረት አለ:: በዛው ልክ ደግሞ ከፍተኛ የሆነ ፍላጎት አለ:: በሁለተኛ ደረጃ መልካም ነጋዴዎች እንዳሉ ሁሉ ሕገወጥ ነጋዴዎች ምርት በመደበቅ የዋጋ ንረት እንዲከሰት በማድረግ ጥቅም የሚያገኙ ነጋዴዎች ለዋጋ ንረትና አጠቃላይ ለኑሮ ውድነት ትልቅ ድርሻ አላቸው::

እንዲህ አይነት ነጋዴዎች በከተማው ምርት በመደበቅ ገበያው ላይ የምርት እጥረት እንዲከሰትና እጥረት ሲከሰት ደግሞ ዋጋ ጨምሮ የመሸጥ አዝማሚያዎችን ያሳያሉ:: በመሆኑም ሀዋሳ ከተማን ጨምሮ በአገር ደረጃ የዋጋ መናር በየቦታው ይታያል:: ይህን ችግር ለመቅረፍም በተለይም የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ንግድና ልማት መምሪያ እንዲሁም የኅብረት ሥራ ልማት ጽሕፈት ቤት የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል::

ለአብነትም አላስፈላጊ የዋጋ ንረት እንዲከሰት በሚያደርጉ ሕገወጥ ነጋዴዎችን በመከታተልና በመቆጣጠር እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል ያሉት አቶ ጴጥሮስ፤ በሀዋሳ ከተማ 80 የሚደርሱ ሸማቾችና ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚገኙ መሆኑን ገልጸው የኅብረት ሥራ ማኅበራቱም የተደራጁበትን ዓላማ ለማስፈጸም እየሠሩ መሆኑን ተናግረዋል:: ኅብረተሰቡን ለማገልገል የተደራጁት እነዚህ የኅብረት ሥራ ማኅበራትም በተቻለ መጠን የግብርና እንዲሁም የኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ማቅረብ እንዲችሉ የተጀመሩ ሙከራዎች አሉ:: ሙከራዎቹን አጠናክሮ ለመቀጠልም እየተሠራ ነው::

በዋናነት የአቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን ለኑሮ ውድነቱ አይነተኛ ድርሻ ያለው ቢሆንም ማኅበራቱ የግብርና እንዲሁም የኢንዱስትሪ ምርቶችን ባላቸው አቅም ማቅረብ እንዲችሉ እየተደረገ ይገኛል:: ለአብነትም በሀዋሳ ከተማ አንድ ኪሎ ሙዝ 40 ብር ሲሸጥ የነበረ ሲሆን በአርባምንጭ ዙሪያ የሚገኙ አልሚዎችን






**የኅብረት ሥራ ማኅበራት የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ማቅረብ እንዲችሉ የተጀመረ ሙከራ አለ፤**

በማሰባሰብ በሀዋሳ ከተማ 20 የተለያዩ ቦታዎች ላይ ድንኳኖችን እንዲጥሉና መሸጫ ሼዶችን በማዘጋጀት ሙዝ በ28 ብር መሸጥ እንዲችሉ ማድረግ ተችሏል:: በዚህም በከተማ ውስጥ ሲሸጥ ከነበረው 12 ብር ቅናሽ በማድረግ ገበያውን ማረጋጋት ተችሏል:: ይህ ሥራ በተሰራበት ማግስት አብዛኛው ነጋዴ የሙዝ ዋጋን ከ40 ብር ወደ 30 እና 35 ብር የማውረድ ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ::

በአሁን ወቅት በከተማዋ በተለያዩ አካባቢዎች በድንኳን ውስጥ አንድ ኪሎ ሙዝ በ30 ብር እየተሸጠ ይገኛል:: በዚህም ማኅበረሰቡ ደስተኛ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ጴጥሮስ፤ ሙዝ ላይ የተሠራውን ሥራ መነሻ በማድረግ እንደ ሀዋሳ ከተማ ከዚህ ቀደም በሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ተከፋፍሎ የማያቀውን የስንዴ ዱቄት እያከፋፈለ ይገኛል። ጽሕፈት ቤቱ 1800 ኩንታል የስንዴ ዱቄት በመረከብ አንድ ኪሎ የስንዴ ዱቄት በ40 ብር ሂሳብ ለሸማቹ እያቀረበ ይገኛል:: ውጭ ላይ የሚሸጠው 50 እና 52 ብር ሲሆን በዚህም ከ10 እስከ 12 ብር ባነሰ ዋጋ የቀረበ መሆኑን አንስተዋል::

በዚህ መሠረት የኑሮ ውድነት የተጫነውን ኅብረተሰብ እያገለገሉ እንደሆነ ያነሱት አቶ ጴጥሮስ፤ ፓስታ ፣ማኮሮኒን ጨምሮ ሌሎችንም የፋብሪካ ምርቶችን እንዲሁም የግብርና ምርቶችን በማኅበራቱ አማካኝነት በተመጣጣኝ ዋጋ ለማኅበረሰቡ እያቀረቡ እንደሆነ ነው የጠቀሱት :: በተለይም ሽንኩርት፣ ቲማቲምና ሌሎች አትክልቶችን ጨምሮ በቀጥታ ከአርሶ አደሩ ወደ ሸማቹ እንዲደርስ በማድረግ እየሠሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ ነገር ግን አቅርቦት የችግር ማነቆ እንደሆነባቸው አብራርተዋል::

ከፋብሪካ ምርቶች መካከል የዘይት ምርት ላይ የሚታየው እጥረት ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ ሊሻገሩት እንዳልቻሉ ያነሳሉ። በቅርቡ ሶስት መቶ ሺ ሊትር የሚጠጋ ዘይት ያቀረቡ ቢሆንም አሁንም ድረስ ፍላጎትና አቅርቦቱ ሊጣጣም እንዳልቻለ ነው የገለጹት:: በተለይም መጪው የበዓል ወቅት እንደመሆኑ ሌሎች የምግብ ሸቀጦችን ጨምሮ ዘይት በከፍተኛ መጠን የሚፈለግ በመሆኑ ይህንኑ ፍላጎት ለማሟላት ጥረት ይደረጋል:: በአሁን ወቅትም ከውጭ የሚገቡ የዘይት ምርቶች ሱቅ ላይ እስከ 1200 ብር እየተሸጠ ሲሆን በኅብረት ሥራ ማኅበራት ውስጥ ደግሞ 950 ብር ድረስ ይሸጣል::ሆኖም በቂ አቅርቦት የለም።

ማኅበራት ለትርፍ ያልተደራጁ እንደመሆናቸው ምርቶቻቸውን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ማቅረብ እንዲችሉ የተለያዩ ድጋፎች ይደረግላቸዋል የሚሉት አቶ ጴጥሮስ፤ የቦታ የትራንስፖርትና ሌሎች ድጋፎችንም በማድረግ ማኅበራቱ ውጭ ላይ ካለው ዋጋ በተወሰነ መጠን ቅናሽ ድርገው ገበያውን ማረጋጋት እንዲችሉ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል:: ይሁንና እንደ ከተማ አስተዳደር ይበልጥ መሥራት የሚገባውና በተለይም ያለአግባብ ዋጋ የሚጨምሩ ነጋዴዎችን ከመቆጣጠር አንጻር የሚቀሩ ሥራዎች እንዳሉ ጠቁመዋል:: ከዚህ ጋር በተያያዘም ሸማቹ ማኅበረሰብም በሁሉም ነገር መንግሥትን ብቻ የመጠበቅ አዝማሚያዎች ያሉት በመሆን ይህ አይነቱ አመለካከት መቀየር እንዳለበት አንስተው ማኅበረሰቡ የሚያጋጥመውን ማንኛውም ሕገወጥ ድርጊት የማጋለጥ ሥራ መሥራት እንዳለበት አመላክተዋል::

መጪው ጊዜ የበዓል ወቅት እንደመሆኑ በርካታ ሥራዎች መሥራት የሚጠይቅ መሆኑን ያነሱት አቶ ጴጥሮስ፤ ከግብርና እንዲሁም ከኢንዱስትሪ ምርቶች በተጨማሪ ወተትና የወተት ተዋጽዖ እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽዖዎችን ያቀርባሉ። ለአብነትም በቅርቡ ከስምንት ብር በላይ ሲሸጥ የነበረው እንቁላል እስከ ስድስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም መሸጥ የቻሉ ሲሆን አይብ ቅቤና መሰል የወተት ተዋጽዖም በአርብቶ አደሮች አማካኝነት እየቀረበ ይገኛል:: በመሆኑም በአሁን ወቅት አንድ ኪሎ ቅቤ እስከ በ550 ብር እየተሸጠ ነው :: ይህንኑ አጠናክረው መቀጠል ከተቻለ በቀጣይ ገበያውን ማረጋጋት እንደሚቻል አስረድተዋል::

ለዋጋ ንረት ዋነኛ ማነቆ የሆነውን የምርትና የአቅርቦት እጥረት ለማሻሻል ለአርሶ አደሩም ሆነ ለኢንዱስትሪዎች ምን ድጋፍ አድርጋችኋል? ምንስ መደረግ አለበት ስንል ላነሳነው ጥያቄ አቶ ጴጥሮስ ሲመልሱ፤ የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር በከተማዋ ዙሪያ ከመስኖ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የተለያዩ ድጋፎች እያደረገ ነው። በተለይም ከግብርና ምርቶች ጋር ተያይዞ ለአርሶ አደሩ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘርና ሌሎችንም አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ይቀርባሉ:: ይበልጥ ደግሞ በአሁን ወቅት እንደ አገር የተጀመሩ ንቅናቄዎችን ለማስቀጠል ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ::

ይህም ሲባል እያንዳንዱ ሰው ትንሽም ቢሆን ባለው ቦታ ላይ ምግብ ሰብሎችን እንዲያለማ በማድረግ የከተማ ግብርና እንዲስፋፋ ማድረግ ነው:: በተለይም በሃይማኖት ተቋማት፣ በትምህርት ቤቶችና ሰፋፊ ይዞታዎች ባሉበት አካባቢ የከተማ ግብርናን አጠናክሮ መቀጠል እንዲቻል እየተሠራ ነው:: ይህን አጠናክሮ መቀጠል ከተቻለ የሚታየውን የአቅርቦት ችግር ማቃለል ይቻላል በሚል ዕምነት ወደ ተግባር መገባቱን ጠቁመዋል::

የፋብሪካ ምርቶችን በተመለከተም እንዲሁ አምራቾች ከደላላ ውጭ ሆነው ምርቶቻቸውን በቀጥታ ሸማቹ ጋር ማድረስ የሚችሉበትን መንገድ እየተዘረጋ ነው:: ለዚህም በከተማ ውስጥ የመሸጫና የማከማቻ ቦታዎችን ከክፍያ ውጭ በሆነ መንገድ የማዘጋጀትና የመደገፍ ሥራ ይሠራል:: አምራቾች ያለምንም ችግር በቀጥታ ለሸማቹ ማቅረብ ከቻሉ መሐል ላይ ሆኖ ዋጋ እየጨመረ ያለውን ደላላ ከጫወታ ውጭ በማድረግ ገበያውን ማረጋጋት የሚያስችል መሆኑ ታምኖበት እየተሠራ ነው::

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተወሰደ ተሞክሮም የእሁድ ገበያን ተግባራዊ ማድረግ መቻሉን ያነሱት አቶ ጴጥሮስ፤ በአሁን ወቅት ሁለት አርሶ አደሮች በዋናነት ቲማቲም፣ ሽንኩርትና ጥቅል ጎመን ለሸማቹ በቀጥታ እያቀረቡ ይገኛሉ ብለዋል:: የመሸጫ ቦታውን ኪራይ ከመሸፈን ባለፈም ጥበቃ በማድረግ ምርቶቻቸውን በቀጥታ ለሸማቹ ማቅረብ እንዲችሉ ተደርጓል:: ከፋብሪካዎች ጋርም በተያያዘ በተለይም የሳሙና ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾች የመሸጫ ቦታ በማመቻቸት ሸማቹም ሆነ አምራቹ ተጠቃሚ እንዲሆን የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ቢሆንም የተሟላ ነው የሚል ዕምነት የሌላቸው በመሆኑ ተጠናክሮ የሚቀጥል ነው::

ከተደራሽነት አንጻር እንደ ሀዋሳ ከተማ ስፋት ገና ብዙ የሚቀር ሥራ መኖሩን ይናገራሉ አቶ ጴጥሮስ። ስምንት ክፍለ ከተሞችና 32 ቀበሌዎች ላሏት ሀዋሳ ከተማ ሥራው ገና ጅምር መሆኑን አንስተዋል:: በመሆኑም ሥራውን አጠናክረው ለመቀጠል አርሶ አደሩን በመቀስቀስ በቀጣይ በስፋት የሚሠራ ይሆናል::

እንደ አገር የሚታየው የኑሮ ውድነት ረገብ እንዲል ብሎም ገበያውን ማረጋጋት እንዲቻል በሀዋሳ ከተማ ኅብረት ሥራ ማኅበር በኩል የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛል:: ከእነዚህም መካከል ከእሁድ ገበያ በተጨማሪ በየዕለቱ በስምንቱም ክፍለከተሞችና በ32 ቀበሌዎች የተለያዩ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶች በሸማቹ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አማካኝነት ለሸማቹ እየቀረበ ይገኛል::

ለዋጋ ንረት መባባስ ጉልህ አስተዋጽኦ ያላቸው ነጋዴዎችን ላይ እርምጃ በመውሰድ ለማስተካከል በተደረገው ክትትልና ቁጥጥር 147 ቤቶች የታሸጉ መሆናቸውን ለአብነት አንስተዋል። በሕገወጥ መንገድ ሲዘዋወር የነበረ ሶስት ሺ ሊትር ቤንዚንም እንዲሁ ተወርሶ ለመንግሥት ገቢ መደረጉ ከማስተካከያ እርምጃዎች መካከል የሚጠቀሱ ነው :: በቀጣይ ሶስት ወራት ውስጥ እንደ ከተማ አስተዳደር በርካቶች እየተማረሩበት ያለውን የቤንዚን ንግድ ላይ ያለውን ችግር ለማስተካከል እየተሠራ ነው::

ሕገወጥ የንግድ ቤቶችን ከማሸግና እርምጃ ከመውሰድ ባለፈ የሸማቾችና ኅብረት ሥራ ማኅበራትን አቅም በመገንባት ኅብረተሰቡ አማራጭ ማግኘት እንዲችል በማድረግ እየተባባሠ የመጣውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት መሥራት አማራጭ የሌለው ምርጫ በሆኑ የተጠናከረ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል ::

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ‹‹ዛፉ››

ኃይሉ ሣህለድንግል

በዓለም የቁመተ ረጅም ነገር ሲነሳ ብዙ የሚባል አለ:: በአገራችን ረጅም ቁመት ያለው መለሎ፣ ዘንካታ፣ ብቅል አውራጅ፣ ወዘተ እየተባለ ይጠራል:: ብቅል አውራጅ መባሉ ከምድጃ በላይ ከጣራ ስር የሚሰቀለውን ብቅል ያለምንም መወጣጫ ለማውረድ የሚችል በመሆኑ መሰለኝ::

በዓለማችን ሰባት ባለረጃጅም ቁመቶች በጊነስ ቡክ ተመዝግበው ይገኛሉ:: በሕይወት ካሉት መለሎዎች መካከል ደግሞ አንዱ ቱርካዊው ሱልጣን ኮሰን ነው:: ሱልጣን ኮሰን አርሶ አደር ነው:: እአአ ታህሳስ 10 ቀን 1982 የተወለደው ይህ መለሎ፣ 251 ሴንቲ ሜትር ይረዝማል፤ በአሁኑ ወቅትም ከጤና ጋር በተያያዘ ክራንች የሚጠቀም ሲሆን ፣ የዓለማችን ሰባተኛው ቁመተ ረጅም በመባልም ይታወቃል::

ወደ አገራችን ስንመጣ ደግሞ አስራት ፋና ለዓመታት በረጅምነት ሲጠቀስ ኖሯል:: በቅርቡ ደግሞ በምስራቅ ሸዋ መቂ አንድ መለሎ ስለመኖሩ መገናኛ ብዙኃን አስተዋውቀውናል:: ከዚህ ብዙም ሳይቆይ ደግሞ ከወደ አማራ ክልል ሌላ መለሎ ተገኝቷል፤ ብርሄ ጋሹ ይባላል::

መለሎው በአዊ ዞን አዲስ ቅዳም ወረዳ ድማማ እንገረፍ የሚባል አካባቢ ነዋሪ ነው:: በቅርቡ የአማራ ክልል እና የፌዴራል መንግሥት ባለስልጣናት በዚህ አካባቢ የበጋ መስኖ ስንዴ እርሻ በጎበኙበት ወቅት የታየው ይህ ሰው የመገናኛ ብዙኃን ቀልብ ስቦ ሰንብቷል:: እኔ ደግሞ ጎጃምም ሳልሄድ ደጄ መጣልኝ፤ በፈረስ ሲሉት በእግር እንደሚባለው:: የምኖርበት አካባቢ ጥቁር እንግዳ ሆነ፤ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ጎፋ መብራት ኃይል ኮንደሚኒየም መንደር፤ ቀረብኩት፤ ብዙ አወራን::

በአካባቢው ሰዎች መሐል ሆኖ ሲራመድ ለተመለከተው ለአንዳንድ ዝግጅቶች በእንጨት ላይ ቆመው በዋና ዋና ጎዳናዎች የሚዘዋወሩ የበዓል አድማቂዎችን ይመስላል:: ሁሉም ሽቅብ የሚመለከተው ተጨዋችና ግልጽ ነው:: እድሜው 40 ሳይሞላው እንደማይቀር ይናገራል:: መጀመሪያ እንዳገኘሁት ስለቁመቱ ርዝመት ትክክለኛውን አኃዝ አይታወቅም:: ቁመቱን የለኩት ሰዎች አንዴ ሁለት ሜትር ከ50 ሌላ ጊዜ ደግሞ ሁለት ሜትር ከስልሳ ብለውት ነበር፤ ትናንት በደረሰኝ መረጃ መሠረት ደግሞ ከሰላሳም ከሃምሳም እንደሚሉት ይገልጻል፤ በአኃዙ ላይ አሁንም እርግጠኛ መሆን አልተቻለም:: ክብደቱ አንድ ወቅት ላይ 98 ኪሎ ነበረ፤ አሁን 88 ኪሎ ነው::

እድሜውን ሙሉ ከጫማ ጋር ሳይተዋወቅ ኖሯል፤ ለአርባ ዓመታት ማለት ነው:: ምክንያቱ ደግሞ በልኩ የሚሆን ጫማ አለማግኘቱ ነው፤ በዩቲዩብና በቴሌቪዥን ይዘውት የወጡ የመገናኛ ብዙኃን ያሰራጩትን መረጃ ተከትሎ ግን ከጫማ ጋር ከመተዋወቅ አልፎ ጫማ በጫማ ሆኗል:: ልብስም ቢሆን እንደማንኛውም ሰው ገበያ ላይ አያገኝም፤ በዚህ የተነሳም ሁሌም እያሰፋ ይለብሳል:: ለሙሉ ልብስ ብዙዎች ሁለት ሜትር ከሩብ አካባቢ ቢያስፈልጋቸውም እሱ ግን አራት ሜትር ያስፈልገዋል::

ቤተሰቦቹ እሱን ጨምሮ ስድስት ልጆች ወልደዋል፤ አንዷ ሴት ስትሆን አሁን በሕይወት የለችም፤ ከእሱ በቀር ሌሎቹ ረጅሞች አይደሉም፤ ከቤተሰብ ወይም በዘር ረጅም ሰው ነበር ወይ የሚል ጥያቄ ቀርቦለትም እንደሌለ ነገረን:: አልተማረም፤ ለምን የሚለው ጥያቄ ተከተለ፤ ያው የገጠር ነገር ሲል ወንድሙ መለሰልኝ::

አባቱ በሕይወት የሉም ፤ እናቱ መንኩሰዋል፤ እናቱ ከአጠገባቸው እንዲለይ በጭራሽ አይፈልጉም፤ ሰውም ጉዳይ አርጎ ሲመለከተው ብዙም አይወዱም፤ በስስት ነው የሚመለከቱት:: ወደ አዲስ አበባ እንደሚሄድ ሲሰሙ በጽኑ ተቃውመዋል፤ ብዙ ውይይት ተደርጎ ፈቅደው ጉዞ ወደ አዲስ አበባ መደረጉን ወንድሙም እሱም ይናገራሉ::

ባለትዳርና የአራት ልጆች አባት ነው:: ከልጆችህ መካከል በቁመት አዝማሚያቸው ወደ አንተ የሆነ አለወይ የሚለው ቀጣዩ ጥያቄያችን ነበር:: ሴት ልጁ ገና በአስር አመቷ በጣም ረጅም መሆኗንና የጫማ ቁጥሯም 40 መድረሱን ነገረኝ፤ የስምንት ዓመት ወንድ ልጁም ረጅም ይሆናል የሚል ግምት አለው፤ ይህንንም ‹‹አገዳው የእኔ ነው›› ሲል ገልጾታል:: እንዳለው ከሆነ ቤታቸው የዛፎች ቤት ሊሆን ተቃርቧል ማለት ነው::

ብርሄ፣ የመኖሪያ ቤቱን በር በልኩ ሰርቶ እንደልቡ የሚገባው የሚወጣ ቢሆንም፣ በሄደበት ሁሉ ሽብረክ ጎንበስ ብሎ ይገባል፤ ይወጣል:: በምትሄድበት ቤት እንዴት አርገህ ትወጣለህ ትገባለህ በሚል ለቀረበለት ጥያቄም ‹‹ጠላትን ትጠነቀቃለህ አይደል›› ሲል መለሰ::

በመኝታ በኩልም በቤቱ ችግር የለበትም፤ በልኩ አልጋ አሰርቷል፤ በሚሄድበትም ብዙም ችግር ገጥሞት አያውቅም፤ በመስተንግዶ እድለኛ ነው:: አስተናጋጆቹ ለእግሩ የሚሆን እንደ ወንበርና የመሳሰሉትን ቁሳቁስ ከአልጋው ግርጌ ያደርጉለታል፤ እዚያ ላይ እግሩን ይዘረጋል:: ሆቴል ቤት ግን ይቸገራል፤ አዲስ አበባ እንደመጣ ያደረበት ሆቴል ቤት ባለቤት ሁኔታውን አይቶ ለመኝታ ክፍሉ ባዘጋጀለት ክፍል ተጨማሪ አልጋ ዘርግቶ እንዳስተኛውና በቀጣይ ለእንደዚህ አይነት ሰዎች ልዩ ክፍል ማዘጋጀት እንዳለበት መናገሩንም ገለጸልኝ::

ቁመትህን የሚመለከተው የአካባቢው ሰው ምን ይልሃል? የሚል ጥያቄ ተከተለ:: ‹‹ወልተረዥ›› ይሉኛል ሲል መለሰ:: ወልተረዥ ማለት? ቀጣዩ ጥያቄ ሆነ:: አብሮት የነበረው ወንድሙ ገብሬ ‹‹ዛፉ›› እንደ ማለት ነው አለ::

የሕዝብ ፍቅር ግን አለው:: ከተማ ወጣ ማለት ጋባዡ ብዙ ነው:: ትራንስፖርት ላይም እንደዚያው:: ችግሩ ወንበር ላይ ቢሆንም፣ አስቀድሞ ለጉልበቱ የሚመቸውን ዳርቻ ይመርጣል::

ብርሄ የሚተዳደረው በግብርና ሥራ ነው፣ ግብርናው ግን ፈትኖታል፤ ከእርፉ ጋር መስማማት አልቻለም፤ እርፉን ለእሱ እንዲመቸው ሲያደርግ በሬዎች እንደሚጎዱበት፣ የእነሱን ደህንነት ሲጠብቅ ደግሞ እሱ ዝቅ ብሎ ለመሥራት እንደሚቸገር ይናገራል:: በአረሙም በአጨዳውም እንደዚያው ነው፤ ጉልበቶቹ የሚሠራውን ይሸፍኑበታልና:: በ1989 ዓ.ም ክልሉ መሬት ለአርሶ አደሮች ሲያከፋፍል እሱ ገና ልጅ ነበርና እንደ ሌሎች አርሶ አደሮች በቂ የእርሻ ቦታ የለውም::

ቀጣዩ ጊዜ ግን ይበልጥ ፈተና እንደሚሆንበት ብርሄ ያመለክታል:: ቁመቱና ክብደቱ ያልተጣጣሙ መስሎኝ ምነው ክብደትህ አነሰ ስል ጠየቅሁት፤ ኑሮ ያልተመቻቸለት መሆኑን ገለጸ:: ምግብ ብዙም አይደፍርም፤ ወንድሙም ይህን ይመሰክራል፤ ከእሱ ይልቅ እኛ ብዙ እንመገባለን ይላል:: በሚጠጣ ላይ ግን የሰጠው እንደሚደክመው ነው የተናገረው፤ ጠላ ጠጥቶ አይጠግብም፤ እንኳንም ጎጃም ተወለደ::



ብርሄ ጋሹ

እድሜው እየጨመረ ሲሄድ ግብርናው ይበልጥ እንደሚያስቸግረው የሚናገረው ብርሄ፣ ወረዳውና ክልሉ የሚተባበሩት ከሆነ ከተማ አካባቢ ሊሠራ የሚችልበት ሁኔታ ቢፈጠርለት ይወዳል፤ በተለይ ቆሞ የሚሠራው ቢያገኝ ይፈልጋል:: እንደ ከብት ማድለብ፣ እህል በረንዳ ያለ ሥራ ባገኝ ጥሩ ነው ይላል:: እኔም ለትብብር እያመሰገንኩ ፍላጎቱ ይሙላለት ብያለሁ::

# ዓለም አቀፍ

## የዩክሬኑ ጦርነት የዓለም ኢኮኖሚ እድገትን በግማሽ ሊቀንሰው እንደሚችል የዓለም ንግድ ድርጅት ገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር




በዩክሬን የተቀሰቀሰው ጦርነት በዘንድሮው የፈረንጆቹ ዓመት የሚካሄደው ንግድ የዓለም የንግድ ድርጅት (ደብሊው ቲ ኦ) በፈረንጆቹ ባለፈው ጥቅምት ወር ከተነበየው 4.7 በመቶ እድገት በግማሽ በመቀነስ ወደ ከ2 ነጥብ 4 እስከ 3 በመቶ ዝቅ ሊል ይችላል ብሏል::

የንግድ ድርጅቱ እንደገለጸው ሩሲያ እና ዩክሬን ወደ ተለያዩ አገራት ይልኩት የነበረው ምርትም ቀንሷል::

የግሎባል ሲሙሌሽን ሞዴል መጠቀሙን የገለጸው የንግድ ድርጅቱ ሴክሬታሪያት ጦርነቱ የዓለም የምጣኔ ሀብት በ0.7 እስከ 1.3 በመቶ እድገት በመቀነስ ወደ 3.7 በመቶ ዝግ ሊደርገው ይችላል ብሏል::

ጦርነቱ ሰብዓዊ ድቀትን ብቻ አይደለም ያስከተለው እንደ ድርጅቱ ሪፖርት:: ይልቁንም የዓለምን የንግድ መጠን ተዛብቷል፤ የዓለም የንግድ ምጣኔ ከመቀነሱም በላይ ከፍተኛ የምግብና የነዳጅ ዋጋ ንረት ማጋጠሙን ገልጿል::

የንግድ ድርጅቱ እንደገለጸው ሩሲያ እና ዩክሬን ወደ ተለያዩ አገራት ይልኩት የነበረው ምርትም ቀንሷል፤ ይህ በዋናነት ደሃ አገራትን ለከፋ ችግር የሚዳርግ ነው:: ፖለቲካዊ መረጋጋትን ሊያሳጣቸውም ይችላል ብሏል ሪፖርቱ::

በሩሲያ እና ዩክሬን መካከል ግልጽ ጦርነት የተጀመረ ሲሆን፤ ከ3 ሚሊዮን በላይ ዜጎች አገራቸውን ለቀው ወደ ጎረቤት አገራት መሰደዳቸውን ዓለም አቀፉ የፍልሰተኞች ድርጅት በሪፖርት ገልጿል።

ሩሲያ ጎረቤቷ ዩክሬን ኔቶን እቀላቀላለሁ ማለቷን ተከትሎ ከፈረንጆች የካቲት 24 ቀን 2022 ጀምሮ ወታደራዊ ዘመቻ ማካሄድ መጀመሯ ይታወቃል።

የዩክሬን ኃይሎች ጠንካራ ተቃውሟቸውን የፈጠሩ ሲሆን ምዕራባውያን ሩሲያ ኃይሏን እንድታስወጣ ከፍተኛ ማዕቀብ ጥለዋል።


የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት(ተመድ) ጠቅላላ ጉባኤ ባደረገው ስብሰባ ሩሲያ ዩክሬንን መውረሯን የሚያወግዘውን የውሳኔ ሀሳብ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል።

ሩሲያ በዩክሬን ላይ ጦርነት የከፈተችው፣የኔቶ ጦር ዩክሬንን ጨምሮ ወደ ቀድሞ የሶቭየት ኅብረት አገራት እየተስፋፋ ነው፤ይህም ለደህንነቷ አስጊ እንደሚሆን በመግለጽ ነበር።የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት እንደቀጠለ ቢሆንም አገራቱ ችግሩን ለመፍታት ውይይታቸውን ጀምረዋል።

የሩሲያ የፍትሕ ሚኒስቴር እንዳስታወቀው የአምነስቲ ኢንተርናሽናልን እና ሂውማን ራይትስ ዎች ጨምሮ የ15 የውጭ ድርጅቶችን ፍቃድ በመንጠቅ ቢሯቸውን ዘግቷል::

ሩሲያ የድርጅቶቹን ፍቃድ የሰረዘችበትን ዝርዝር ምክንያት አለማቅረቧን ሮይተር ዘግቧል::

የሩሲያ ፍትሕ ሚኒስቴር ይህን ውሳኔ ያሳለፈው ዋና መቀመጫውን ኒውዮርክ ያደረገው ሂውማን ራይትስ ዎች ሩሲያ በዩክሬን ባካሄደችው ልዩ ወታደራዊ ዘመቻ የተሳተፉ ወታደሮቿ የጦርነትን ሕግ በመጣስ መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰት አካሂደዋል የሚል ሪፖርት ማውጣቱን ተከትሎ ነው::



## ሸህባዝ ሻሪፍ የፓኪስታን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተመረጡ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የቀድሞው የፓኪስታን ጠቅላይ ሚኒስትር ናዋዝ ሻሪፍ ታናሽ ወንድም የሆኑት ሸህባዝ ሻሪፍ አዲሱ የፓኪስታን ጠቅላይ ሚኒስትር ተደርገው በአገሪቱ ሕግ አውጪ ምክር ቤት ተሹመዋል። አዲሱ ተመራጭ ጠቅላይ ሚኒስትር ጥቅምት 2023 ድረስ በስልጣን ላይ ይቆያሉ ተብሏል፡፡

የፓኪስታኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢምራን ካሃን በአገሪቱ ፓርላማ የመተማመኛ ድምፅ በማጣታቸው ባሳለፍነው ቅዳሜ ከስልጣን መነሳታቸው ይታወሳል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ኢምራን ካሃን አመራር ላይ የመተማመኛ ድምጽ የመስጠት ሂደት የተካሄደው ቅዳሜ እኩለ ሌሊት ላይ ሲሆን፤ ድምጽ የተሰጠው ተቃዋሚዎቻው በእርሳቸው ላይ ሞሽን ካቀረቡ በኋላ መሆኑ ተገልጿል።

የመተማመኛ ድምጽ እንዲሰጥ የሚጠይቀው ሞሽን ባሳለፍነው ሳምንት ቀርቦ የነበረ ሲሆን፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀደም ብለው ፓርላማውን በመበተናቸው ሳይካሄድ ቆይቶ ነበረ።

የአገሪቱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጠቅላይ ሚኒስትር ኢምራን ካሃን ከሕገ መንግሥቱ ውጪ ፓርላማውን በትነዋል በሚል ውሳኔያቸውን ውድቅ ማድረጉን ተከሎም ፓርላማው ተሰብስቦ ድምጽ ሰጥቷል።

ይህንን ተከትሎም ኢምራን ካሃን በፓርላማው የመተማመኛ ድምጽ በማጣታቸው ከጠቅላይ ሚኒስትርነታቸው ተነስተዋል።

ኢምራን ካሃን በፓኪስታን ታሪክ የመተማመኛ ድምጽ በማጣት ከስልጣናቸው የተነሱ የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር መሆናቸውም ተዘግቧል።

የፓኪስታን ፓርላማ ኢምራን ካሃንን ተክተው ጠቅላይ ሚኒስትር የሚሆኑትን ሰው ዛሬ መርጧል።

በኢምራን ካሃን ቦታ የተመረጡት ሸህባዝ ሻሪፍ በአገሪቱ ምርጫ እስከሚደረግበት የፈረንጆቹ ጥቅምት 2023 ድረስ በስልጣን ላይ ይቆያሉ ተብሏል።

የፓኪስታኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢምራን ካሃን ባሳለፍነው ቅዳሜ “ተቃዋሚዎቼ ከአሜሪካ ጋር እያሴሩ ሊገለብጡኝ ነው” ማለታቸው ይታወሳል።

# ስፖርት



## በጥቂት ዕድል እየተገኘ ያለውን ብዙ ውጤት ለማሳደግ

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያ ከሜልቦርን እስከ ቶኪዮ ኦሊምፒክ በተሳተፈችባቸው መድረኮች 23 የወርቅ፣ 12 የብርና 23 የነሐስ በድምሩ 58 ሜዳሊያዎችን መሰብሰቧ ይታወቃል:: ከእነዚህ ውስጥ 22 የሚሆኑት (8 የወርቅ፣ 4 የብር እና 10 የነሐስ) ሜዳሊያዎች በሴት አትሌቶች የተመዘገቡ ናቸው:: በቶኪዮው የ2020 ፓራሊምፒክም በ1ሺ500 ሜትር በአትሌት ትዕግስት ገዛኸኝ ለመጀመሪያ ጊዜ የወርቅ ሜዳሊያ መገኘቱ ይታወሳል::

አትሌቲክስ እግር ኳስ ስፖርቶች እንደማሳያ ተነሱ እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በበርካታ ስፖርቶች በአንጻራዊነት በሴቶች የሚመዘገበው ውጤትና ተሳትፎ እያሻቀበ ይገኛል:: በእግር ኳስ ከ20 ዓመት በታች ሴቶች ብሔራዊ ቡድን ለዓለም ዋንጫ ተሳትፎ ከጫፍ ደርሶ የነበረበትን ሁኔታም እዚህ ሊጠቀስ ይገባዋል:: ይኸውም በተለያዩ የስፖርት ማኅበራት በሚደረጉ አህጉርና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የሴት ብሔራዊ ቡድኖች ተወዳዳሪነት በግልጽ እየታየ ይገኛል::

ይህ የሚያሳየውም በሴቶች ስፖርት ጥቂት በመሥራት ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ መቻሉን ነዉ:: ከዚህ እውነታ በመነሳት፣ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ እንዲሁም የውድድር መድረኮችን በማስፋት ሴቶች የመወዳደር እድል እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የመላ ኢትዮጵያ ሴቶች ውድድር ራሱን ችሎ እንዲካሄድ ተደርጓል::

ከመደበኛ ዓመታዊ ውድድሮች ባለፈ ሴቶችን ብቻ ማዕከል አድርገው በተለያዩ ስፖርቶች መሰል ውድድሮችን ማድረግ በሌሎች ዓለማትም የተለመደ ነው:: በአሜሪካ እአአ ከ1987 ጀምሮ በጥር ወር መጨረሻ የሴቶች ስፖርት ቀን በሚል ውድድሮች ይካሄዳሉ፤ ውድድሮቹ ታላላቅ ሴት ስፖርተኞችን የሚዘክሩና ዕውቅና የሚሰጡ ናቸው፤ ሌሎች የተለያዩ መርሐ ግብሮችንም ማንሳት ይቻላል::



**የውድድር መድረኮችን በማስፋት ሴት ስፖርተኞችን ለበለጠ ውጤታማነት ማብቃት ይቻላል፤**

በኢትዮጵያ የኦሊምፒክ መርሕን መሠረት አድርገው ከሚካሄዱ ጥቂት ውድድሮች መካከል አንዱ የሆነው ይህ ውድድር ዘንድሮ ለ4ኛ ጊዜ እየተካሄደም ይገኛል:: ይህ የመላ ኢትዮጵያ ሴቶች ውድድር በኮቪድ ወረርሽኝ ስጋት ምክንያት ተቋርጦ የቆየ ሲሆን፤ ዘንድሮ በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሃዋሳ ከተማ ከሚያዝያ 01 ጀምሮ እስከ 10/2014 ዓም እየተካሄደ ነው::

በውድድሩ ስድስት ክልሎችንና ሁለት ከተማ አስተዳደሮች ተወካዮቻቸውን እያሳተፉ ቢሆንም የተቀሩት ግን በወቅታዊና ሌሎች ችግሮች ምክንያት አለመካፈላቸውን በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የውድድርና ስልጠና ዳይሬክተር ወይዘሮ አበባ አማረ ይጠቁማሉ:: ውድድር እየተካሄደባቸው ያሉ ስፖርቶችም አትሌቲክስ፣ እግር ኳስ፣ ቮሊቦል፣ ዳርት፣ ጠረጴዛ ቴኒስ፣ ቼስ፣ ፓራሊምፒክ፣ መስማት የተሳናቸው ዊልቸር ቅርጫት ኳስ እንዲሁም የባህል ስፖርቶች ናቸው:: ቁጥራቸው ከአንድ ሺ በላይ የሚሆኑ ስፖርተኞችና አሰልጣኞቻቸውም በዚህ ውድድር ላይ ተካፋይ ናቸው::

ከዚህ ቀደም ከስፖርተኛ ተገቢነት ጋር በተያያዘ ይነሳ የነበው ቅሬታ ለማስወገድም በዚህ ውድድር 10 ከመቶ የሚሆኑ ተሳታፊዎች ከክለቦች፣ ከስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከላት እንዲሁም በዓለም አቀፍ ውድድሮች ከተሳተፉ ስፖርተኞች ተካፋይ እንዲሆኑ ተደርጓል:: ከዚህ ባለፈ ያሉት 90 ከመቶ የሚሆኑ ተወዳዳሪዎች ተተኪ ስፖርተኞች መሆናቸውንም ነው ዳይሬክተሯ የጠቆሙት:: በዚህም ተተኪ ስፖርተኞች ልምድ ካላቸው ጋር ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ከማገዝ ባለፈ ለውጤታማነትም የራሱ ሚና ይኖረዋል ይላሉ::

እንደአገር በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች በተለይ በሴቶች በኩል የተሻለ ውጤታማነት እየታየ መሆኑን የሚያነሱት ዳይሬክተሯ፣ ለስፖርተኞቹ ግን የተለየ እገዛ እየተደረገላቸው አለመሆኑን ይጠቁማሉ::

በዚህ መልኩ ውጤታማ ከሆኑ ደግሞ በአህጉርም ሆነ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ በይበልጥ ስኬታማነታቸውን እንዲያሳድጉ ለማድረግ ጥቂት የውድድር ዕድል ሊፈጠርላቸው እንደሚገባ አመላካች ነው:: በመሆኑም በየስፖርት ዓይነቱ ከሚካሄዱት መደበኛ ውድድሮች ባለፈ የውድድር መድረክ እንዲያገኙ ውድድሩ ይካሄዳል:: ሌላው ውድድሩን ተከትሎ ሚኒስቴሩ ለክለቦች እንዲሁም ለስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከላት ጥሪ ያቀረበ ሲሆን፤ በውድድሩ ስፍራ ተገኝተው ስፖርተኞችን ለመመልመልም አመቺ ይሆናል::

ከውድድሩ ጎን ለጎን ሲምፖዚየም፣ ማኅበረሰብ አቀፍ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ከጾታዊ እኩልነት ጋር በተያያዘ ግንዛቤ የማስጨበጥ መርሐ ግብሮች እየተከናወኑ እንደሚገኙም ነው ዳይሬክተሯ የገለጹት::


### የንግድ ምልክት ዕድሳት ማስታወቂያ

| | | |
|---|---|---|
| 1. | የባለቤቱ ስምና አድራሻ | ዲያጂዮ ኖርዝ አሜሪካ ኢንክ. (Diageo North America Inc.)<br>Three World Trade Center, 175 Greenwich Street, New York, U. S. A., 10007 |
| 2. | የማመልከቻ ቁጥር | FTM/5882/2015 |
| 3. | የዕድሳት ጊዜ | ከ23/02/2022 እስከ 23/02/2029 |
| 4. | የንግድ ምልክቱ | |
| 5. | ባለቤቱ ይህንን የንግድ ምልክት የሚጠቀመው በዓለም-አቀፍ ምድብ 33 በ08/01/2008 ዓ.ም. በአዲስ ዘመን ጋዜጣ Vol.LXXV No.008 በወጣው ማስታወቂያ ከተዘረዘሩት ምርቶች ጋር በተያያዘ ነው:: | |
| 6. | ማንኛውም ግለሰብ ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም - ከባለቤቱ ሳያስፈቅድ በዚህ የንግድ ምልክት በሚገለገል ወይም አስመስሎ በሚሠራ ላይ በሕግ ክስ ይመሠረትበታል:: | |

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-215-5/8/2014 (13/4/2022)

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም :- ስሪ-ማይ ዲጂስታርደስት በዝ<br>የአመልካች አድራሻ:- ወረዳ 03 የቤት ቁጥር -, ቦሌ አዲስ አበባ , ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር :- LTM12004/2014<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን:- 14/07/2014 E.C. | | |
| 3 | ምልክት | 4 | ምልክቱ መግለጫ:-የቃልና ምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት:- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ:- |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ:- 36 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | ሪል እስቴት የማልማት፣ የማከፋፈል እና የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የማልማት ስራዎች(ምድብ 36) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል::ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን:: ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል::

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-215-5/8/2014 (13/4/2022)

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስምና አድራሻ: Eyad Hadi Mesfer Al Thabeti አድራሻ፡ Desk # 08-101-100 - We Work Middle East DWTC Level 8 - The Offices 4, One Central, Dubai World Trade Center, Dubai, United Arab Emirates | | |
| 2 | ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀንና የማመልከቻ ቁጥር<br><br>ማመልከቻቁጥር ETM / 13183 / 2022 ቀን 2022 - 02 - 21 | | |
| 3 | | 4 | የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ መግለጫ: የምስል እና የቃል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት:- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | አለም አቀፍ ምድብ 34 |
| 7 | አለም አቀፍ ምድብ.34 : ቶባኮ፡ሲጋራ፡ ከብሪት | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡ ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ ይህ ጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊን ብረት ባለስልጣን ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን:: ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት የሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል ::የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን:: ቶባኮ፡ሲጋራ ከብሪት፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-215-5/8/2014 (13/4/2022)

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም :- ምንአየ ፓኬጂንግ ኃላ/የተ/የግ/ማ<br>የአመልካች አድራሻ:- ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 1374 , ንፋስ ስልክ ላፍቶ , አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር :- LTM/11908/2014<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን:- 30/06/2014 E.C. | | |
| 3 | ምልክት | 4 | የምልክቱ ግለጫ:-የቃልና ምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት:- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ:<br>(PACKING, PLC) |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ:- 16 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | ወረቀትና የወረቀት ውጤቶችን መፈብረክ (ምድብ 16) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል::ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረትባለ ስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን::ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል::

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-215-5/8/2014 (13/4/2022)

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ምቹ የሥራ ከባቢን ለመፍጠር- የባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ሚና

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

የመንግሥት አገልግሎት መስጫ ተቋማት ምቹ፣ ማራኪና መልካም የሥራ መንፈስ የሚፈጥሩ እንዲሆኑ ይፈለጋል። በተጨማሪ መሥሪያ ቤቶቹ እራሳቸው የሚያስተዳድሩት ሕንፃ እንዲኖራቸው እና ከከፍተኛ የኪራይ ወጪ እንዲላቀቁ ይፈለጋል። ይህን ለማድረግ ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር 569 ተቋማት በራሳቸው ሕንፃ አገልግሎት ሲሰጡ ቀሪው በዓመት ዘጠኝ መቶ ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎ በኪራይ ሕንፃ ውስጥ አገልግሎት ይሰጣሉ። ይህን ለማስቀረት የከተማ አስተዳደሩ የመንግሥት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን በመመሥረት ወደ ሥራ ገብቷል። ለዛሬ በመንግሥት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን የመንግሥት ሕንፃ ማልማት ምድረ ግቢ ማስዋብና ደህንነት ዳይሬክተር የሆኑትን አቶ ጳውሎስ ብርሃኑን እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን እንዲያብራሩልን እንግዳችን አድርገናል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ተቋሙ በ2011 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 64 የተቋቋመ ነው አዲስ በወጣው ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 74/2014 ዓ.ም በድጋሚ ተሻሽሎ ተመሥርቷል። በዚህ መሥሪያ ቤት ውስጥ ሁለት ዘርፍ ያለ ሲሆን እነዚህም ሕንፃና ንብረት ዘርፎች ናቸው። በሕንፃ ዘርፍ ስር ከሚገኙት ሁለት ዳይሬክቶሬቶች መካከል ዳይሬክቶሬታችን አንዱ ሲሆን በዋናነት የመንግሥት አዳዲስ ሕንፃ ማልማት፣ ምድረ ግቢ ማስዋብና ደህንነት የመጠበቅ ተልእኮ ተሰጥቶት የሚሠራ ነው። ሕንፃ ማልማት በዋነኛነት ግንባታ ሲሆን ምድረ ግቢ ማስዋብ ደግሞ በሕንፃዎቹ ዙሪያ ጥሩ የሥራ መንፈስን የሚፈጥሩ የአረንጓዴ ስፍራዎችን መፍጠርን ያካትታል።



**አቶ ጳውሎስ ብርሃኑ፤**

"የመንግሥት አገልግሎት የሚሰጥባቸው ሕንፃዎች ለተገልጋዩ ኅብረተሰብ ሆነ ለአገልጋዩ ሠራተኛ ምቹ መሆን አለባቸው" የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ ከፍተኛ ወጪ የሚፈስበትን የሕንፃ ኪራይ ለማስቀረትን ዋንኛ ግቡ አድርጎ ከመሥራቱም ባሻገር አስተዳደሩ በመንግሥት ተቋማት የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት እንዲሟሉና ምቹ እንዲሆኑ እየሠራ እንደሚገኝ ይገልፃሉ። በተለይ ከተገነቡ ረጅም ግዜ ያስቆጠሩና ምቹ ያልሆኑትን መሥሪያ ቤቶች ምቹ ማድረግ፣ በሠራተኛ ብዛት የተጨናነቁ፣ለሰነድ ማስቀመጥ የማይመቹና በጥቅሉ አገልግሎት ለመስጠት አስቸጋሪ የሆኑትን ጥናት አድርጎ በመለየት የማስፋፊያ ሥራዎች እንዲሠሩ እየተደረገ ይገኛል።

"ይህ ዳይሬክቶሬት የመንግሥት አገልግሎት መስጫ ሕንፃዎች ባሉበት አካባቢ ሁሉ እታች ድረስ መዋቅር በመዘርጋት የማልማት ሥራዎችን ያከናውናል" ያሉት አቶ ጳውሎስ፤በተለይ በአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ላይ ትኩረቱን በማድረግ ለምሳሌ የካፍቴሪያ አገልግሎት በቀላሉ የሚገኝበትንና ሠራተኛውንም ሆነ ተገልጋዩን የማይጉላሉበትን መንገድ ለማመቻቸት እየሠራ መሆኑን ይናገራሉ። ሌላውና ዋንኛው ጉዳይ የሕፃናት ማቆያ ማዕከል በመንግሥት ተቋማት እንዲኖር ማድረግ ነው። ሴት ሠራተኞችም ሆነ ልጆች ያላቸው ሠራተኞች በዚያው ምቹ በሆነ መንገድ ልጆቻቸውን መከታተልና መንከባከብ እንዲችሉም መሰል ግንባታዎችን ያከናውናል። በተጨማሪ የመኪና ማቆሚያና ማጠቢያዎችም እንዲኖሩ በልዩ ትኩረት የማልማት ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። ከዚህ በፊት የተገነቡት በቂ ቦታ ያላቸውና ለማልማት የማይመቹ ቢሆንም ደረጃቸውን እንዲጠብቁ በተለያዩ መንገዶች ሥራዎች እየተከናወኑ ነው። በዋናነት አዳዲስ የሚገነቡት ግን ሁሉንም መስፈርቶች ያሟሉ እንዲሆኑና የተጠቀሱትን ማዕከላት እንዲያሟሉ ዳይሬክቶሬቱ እየሠራ ይገኛል።

"ዋናው ተግባርና ኃላፊነታችን ሕንፃ ማልማት ነው" የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ በተለይ ምቹና ማራኪ እንዲሆኑ የግንባታ ፕሮፖዛሎችን ገምግሞ፣ ፍቃድ ሰጥቶ፣ ዲዛይኑንም ሆነ ግንባታውን ተከታትሎና ተረክቦ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማስተላለፍን ያካተተ እንደሆነ ይጠቅሳሉ። ሌላው የአስተዳደሩን ለኪራይ የሚወጣውን ከፍተኛ ወጪ ለማስቀረት ኅብረተሰቡም እንዳይንገላታ በተለይ በማዕከል ሴክተር መሥሪያ ቤት ሆነው ምቹ ያልሆነ ሕንፃ ውስጥ ተጣበው የሚሠሩትን መሥሪያ ቤቶች (ለምሳሌ የዲዛይን እና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ፣ ንግድ ቢሮ፣ የፋይናንስ ቢሮ ጨምሮ ከ34 በላይ ሴክተር መስሪያ ቤቶች) በአንድ ቦታ ላይ በማድረግ ምቹ ሕንፃ ለማልማት ሥራ ተጀምሯል። የግንባታ ቦታውን የመለየት የይዞታ ማረጋገጫ የመውሰድ ሥራዎች ጎን ለጎን እየተሠራ ሲሆን በቅርቡ ምቹ ወጪ ቆጣቢና ተገልጋይ የማይጉላላበት የሥራ ቦታ እንደሚፈጠር ይናገራሉ።

"ይህ ግንባታ በጣም ልዩና ግዙፍ ነው" ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በዓይነቱ የመጀመሪያና በተቋሙ ስር የግንባታ ፕሮፖዛሉ መዘጋጀቱን ይገልፃሉ። ሆኖም ግንባታውን የትላልቅ ፕሮጀክት ግንባታ ጽሕፈት ቤት የሚያሠራው ሲሆን መሬቱን ሙሉ ለሙሉ ሕጋዊ አድርጎ ወደ ሥራ ለመግባት አስፈላጊ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ይናገራሉ። ይህ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ ከ34 በላይ መሥሪያ ቤቶች የሚገቡና በተቀላጠፈ ሁኔታ ማኅበረሰቡን እንዲያስተናግዱ ያስችላቸዋል።

በከተማ አስተዳደሩ ስር ይህ ባለስልጣን መሥሪያ ቤት ከመመሥረቱ በፊትና ከተመሠረተም በኋላ ግንባታ ላይ ያሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አሉ። ለምሳሌ ያህል የንፋስ ስልክ ክፍለ ከተማና የልደታ ክፍለ ከተማ፣ የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ እና ሌሎችም ይገኙበታል። እነዚህ በግንባታዎች ምንም እንኳን በመንግሥት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን የመንግሥት ሕንፃ ማልማት ምድረ ግቢ ማስዋብና ደህንነት ዳይሬክቶሬት ይሁንታ ባይጀመሩም በፍጥነት እንዲጠናቀቁ ይሠራል፡፡ ኪራይ ውስጥ ያሉ መሥሪያ ቤቶች ወደ አስገነቡት ሕንፃ ገብተው ወጪን እንዲቀንሱ ብሎም ምቹ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ እየተሠራ ነው።

ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር
ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የዕደ ጥበብ ምርት ልማት ሲባል?

**እየሩስ ተስፋዬ**

ከሚዳሰሱ የባህል መገለጫ አንዱ የዕደ ጥበብ ሲሆን፣ የዕደ ጥበብ ውጤቶችም የተለያዩ ባህሎችን ለማስተዋወቅ፣ መልካም ገጽታን ለመገንባት፣ የማኅበረሰቡ ማንነትና በጐ በጐን በማሳየት ለአካባቢው እና ለማኅበረሰቡ ከበሬታን እንዲያተርፉ ያደርጋሉ።ከዚህ በተጓዳኝም ማኅበራዊ መስተጋብርና መቀራረብን በማሳደግ፣ የኅብረት መንፈስን በማጎልበት አዎንታዊ አስተዋጽኦም አላቸው፡፡

የዕደ ጥበቡን ዘርፍ ስናይ ደግሞ በሁለት መሠረታዊ በሆኑ መንገዶች ይከፈላሉ።አንደኛው የምርቱ ግብዓት የተሠራበት ጥሬ እቃ መሠረት በማድረግ የቅል፣ የቀንድ፣ የጥጥ፣ የእንጨት፣ የስንደዶ፣ አለላ፣ አፍቾ በማለት የሚመደብ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ምርቶቹ ላይ ባረፉባቸው ዲዛይን መሠረት የሚመደቡ ናቸው።እነዚህም ምንም ለውጥ ሳያደርግባቸው ትውፍታዊ በሆነውን ዲዛይን፣ ትውፊትና ዘመናዊ ዲዛይኖችን የያዘ እና ቀድመው ከተጠቀሱት ውጭ የሆነ ሙሉ በሙሉ ዘመናዊነትን የያዙ ተብለው ሊቀመጡ ይችላሉ።

የዕደ ጥበብ ምርቶች ከሌሎች ምርቶች የሚለዩበት ልዩ ባህሪያቸው እና መገለጫቸው የሚመነጨው ከመገልገያነት፣ ከስነ-ውበት፣ ከፈጠራ፣ ከባህል፣ ከጌጣጌጥ ከትውፊት ጋር በተያያዘ ያለው ትስስር ሲሆን፣ ሃይማኖታዊ እና ማኅበራዊ ትዕምርት ሆኖ የሚያገለግል ነው።ምርቶቹ ከስነ ውበት ባሻገር ለመገልገያነት መዋላቸው ልዩ ያደርጋቸዋል።በመሆኑም በእሴት ሰንሰለቱ ያሉ የምርት አምራቾች በየጊዜው የሚፈጠረውን እና እየጨመረ የመጣውን የተጠቃሚውን የምርቶች ፈላጊነት ለማርካት እና ተወዳዳሪነት ለማሳደግ በምርቱ ላይ እሴቶችን በመጨመር የዕደ ጥበቡ ምርት በተለያዩ መንገዶች ማሳደግ ተገቢ ነው፡፡

የዕደ ጥበብ ምርት ልማት ማሳደግ ማለትም ምርቱ በጥራት፣ በብዛት፣ ተደራሽነትን በማስፋት እና በዋጋም ሁሉን ያማከለ ማድረግ ማለት ነው።የዕደ ጥበብ ዘርፍ የምንለው በጣም ብዙ ሰፊ የሆነ የምርት አይነቶች የያዘ ሲሆን፣ ከነዚህ ዘርፎች በአገራችን በሰፊው አገልግሎት ላይ እየዋለ ያለ የሽመና ውጤት የሆኑትን የባህል አልባሳትን ለአብነት ያህል ብናነሳ የዚህን ምርት ልማት ለማሳደግ ከዚህ ቀጥሎ የሚነሱት ጉዳዮች አስፈላጊ ናቸው።እነርሱም፡-

### የሽመና ውጤት የሆኑ የባህል አልባሳት ምርቶችን ማሳደግ

የሽመና ውጤቶች በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል። የመጀመሪያው ሥራው ቀጣይ እሴት የሚጨመርበት በጋርመንት ተጨማሪ ሂደቶችን የሚያልፍ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሽማኔው ካጠናቀቀ በኋላ በቀጥታ ወደ አገልግሎት የሚገባ ነው።ለአብነት ያህል ቡሉኮ፣ ጋቢ፣ ነጠላ እና ቀሚስ መጥቀስ ይቻላል።ታዲያ እነዚህ የባህል አልባሳት ምርት ሆነው እስኪወጡ የብዙ አካላት ሚና የሚፈልጉ ናቸው።ይህም በዘርፉ ያለው የእሴት ሰንሰለቱን ሂደት ምን ያህል ሰፊ እና የብዙ አካላት ተሳትፎ እንዳለበት የሚያመላክት ነው።የባህል አልባሳት የእሴት ሰንሰለት ማለት አንድ ምርት ወይም አገልግሎት ለተጠቃሚ እስኪደርስ በቅደም ተከተል የሚከወኑ ሥራዎች ናቸው።ይህም የሚያካትተው የጥሬ ዕቃ ወይም ግብዓቶች አቅርቦት፣ ምርትን የማምረት ሂደት፣ ዲዛይን፣ የማሸግ፣ የማጓጓዝ፣ የመሸጥና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ሥራዎች ናቸው።ከምርት ወይም ከአገልግሎት የሚያገኘው ጥቅም ሲሆን፣ እሴት መጨመር ማለት በእሴት ሰንሰለቱ ያሉ አካላት በየደረጃው በምርቱ ወይም በአገልግሎቱ ላይ ተጠቃሚው የሚያገኘውን ጥቅም ለማሳደግ የሚደረግ አስተዋፅዖ ነው።በመሠረታዊነት የምርቱን ጠቀሜታ ለማሳደግ መሠራት የሚገባቸው ጉዳዮች ስናይ ደግሞ

### የማምረቻ ግብዓቶች ማሻሻያ

የባህል አልባሳት አምራቾች በቴክኖሎጂ ሽግግር በከፊል በእጅ የሚሠሩ ሥራዎችን የሚያፋጥኑና ድካምን የሚቀንሱ መሣሪያዎች እንዲገለገሉ ይደረጋል፤ በቱሪዝም ተኮር ዕደ ጥበብ ልማት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ያሉ የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት እንደ እርሾ እንዲያገለግሉ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ድጋፍ ዲዛይን ጥናት ይሠራል።የዕደ ጥበብ አምራቾች የሚፈልጓቸውን የአገር ውስጥና የውጭ የማምረቻ መሣሪያዎች በጥናት በመለየት በብድር አቅርቦት እና በሊዝ መልክ እንዲያገኙ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ፣ የቴክኖሎጂ መረጣ እና ልማት፣ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ እና ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ልምዶች ቅመራ እና ጥቅም ላይ የማዋል ሥራዎች መሥራት ናቸው፡፡

### የጥሬ ዕቃ ጥራት እና አቅርቦት ማሻሻያ

ለምርቶች ጥራት እና በተፈለገው ብዛት ማምረት እንዲቻል ጥራቱን የጠበቀ እና ተፈላጊውን የጥሬ እቃ አይነት እንዲሁም የብዛት መጠን በተፈለገው ጊዜና መጠን ማቅረብ የሚችሉ ጥሬ እቃ አቅራቢዎች ማኅበራትን ማቋቋም፣ አምራች ማኅበራት ከማምረቱ ሥራ በተጨማሪ በቀጥታ ጥሬ ዕቃ በማቅረብ እንዲጠቀሙ ለማስቻል የዘርፉ ኢኮኖሚ የጠቀሜታ ስርጭት መጠን እንዲስፋፋ ማድረግ፣ ከውጭ የሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች በተቀላጠፈ እና አቅምን ባገናዘበ መልኩ ለአምራቾች የሚደርሱበት ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታ ከመፍጠር ጐን ለጐን የተመረጡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም በጥሬ ዕቃዎች ጥራት እና ምርታማነት ላይ የማያቋርጥ ጥናት እና ምርምር በማድረግ ውጤቶቻቸውን የሚከታተሉበትና የሚያሰርጹበት ሥርዓት መፍጠር፣ ጥሬ እቃ አቅርቦት ላይ ችግር ሊፈቱ ከሚችሉ የአገር ውስጥ ፋብሪካዎች ጋር በቅንጅት መሥራት ነው፡፡

### የምርት ዲዛይን ማሻሻያ

በምርት ዲዛይንና ማሻሻል እንዲሁም በተለያዩ ዲዛይን ዙሪያ በምርት ዘርፉ ለተሰማሩ የባህላዊ ዕደ ጥበብ ባለሙያዎች ዕውቀቱን በስልጠና ማካፈል፣ ብቃትና ጥራት እንዲኖራቸው ማድረግ፣ አዳዲስ የምርት ዲዛይኖችን በዕደ ጥበቡ ዘርፍ በማዘጋጀት፣ የአገሪቱ ዕደ ጥበብ መስክ የምርት ዓይነቶችና የፕሮጀክት መስመሮች ማዘጋጀት፣ በሽያጭ ላይ ያሉትን የምርት ዓይነቶች ተበራክተው ሽያጫቸው ለረጅም ዓመታት እንዲቆይ ልዩ ልዩ ማሻሻያዎችን በየጊዜው በማጥናት ማሻሻል፣ የፓኬጅ፣ የሌብሊንግና ዲዛይን ሥራዎችን በመሥራት አምራች ዘርፎችን መደገፍ፣ በኤግዚቢሽንና ትሬድፌር ተሳትፎ ወቅት የሚያስፈልጉ የዲዛይን አገልግሎት መስጠት፣ በዘርፉ ሊመረቱ የሚችሉ በተለይም የአገራችን ባህል የሚገልጹ ሆነው ግን በተለያዩ መንገዶች ከውጪ አገራት እየገቡ ያሉ ምርቶችን በአገሬው እንዲተኩ ለማድረግ የመለየት፣ የናሙና ምርት ተመርተው የገበያ ጥናት በማድረግ ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ የሚረዳ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣ ሁሉን የዘርፍን ተዋንያን እና ባለድርሻዎችን ተቀራርቦ መሥራት ብሎም ማሳደግ ለምርት እድገት እና ልማት ወሳኝ ናቸው።

Telegram https://t.me/ministry ofcultureandtourism
Facebook https://www.facebook.com/cultureandsportethiopia